
ግንቦት 2014
ቅጽ ፪ ቁጥር ፩


# ንስንስ

ትኩረቷን በLBTQ ላይ አድርጋ በየሩብ ዓመቱ የምትታተም መጽሔት
Nisnis - Quarterly magazine focusing on LBTQ issues



አታሚ/Publisher
QUEER ETHIOPIA
ኲዊር ኢትዮጵያ

# የፍቅር ግንኙነቶች




# የራስዎን ድምፅ ያድምጡ

www.soundcloud.com/ethioqueer

# ንስንስ

ቅጽ ፪ ቁጥር ፩


በየሩብ ዓመቱ የምትታተመው ንስንስ
በኢትዮጵያ እና በዳያስፖራ የሚገኙ LBTQ
ጉዳዮች ላይ የምታተኩር መጽሄት ናት።

ለጥያቄዎች :
etqueerfamily@gmail.com

በኲዌር ኢትዮጵያ የታተመ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
© ግንቦት 2014

## ማውጫ

| | |
|---|---|
| 3 | የአርታዒያን መልዕክት |
| 4 | በፍቅር ታዛ ስር |
| 14 | ለፍቅራችን ህያልነት |
| 19 | የፍቅር ግንኙነት ． የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነት |
| 20 | ማስታወሻ ለመጀመሪያ ፍቅሬ |
| 24 | የከፍታ ውጊያ፡ መስህብን መረዳት |
| 30 | ከሴት ተመሳሳይ ጾታ ፍቅር ግንኙነት መውጣት ፥ ጓደኝነትን ማስቀጠል |
| 34 | ስለ አንድ ለአንድ ስላልተወሰነ ትዳር |
| 37 | የፍቅር አጋር የት ልናገኝ እንችላለን? የምንፈልገውስ ምን አይነት የፍቅር ግንኙነት ነው? |



# QUEER ETHIOPIA

# ኲዊር ኢትዮጵያ

«ኲዊር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኲዊር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኲዊር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኸውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሸዋል ወይም ኤሴክሸዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኲዊር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ' ኲዊር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ- መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ-መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሳይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።

queerethiopia.com

ethioqueer

QueerEthiopia

etqueerfamily@gmail.com

# የአርታዒያን መልዕክት

“እንደማንኛውም የሀበሻ ጥንዶች ነን” ስትል ፍፁም አብራት ከምትኖረው የስምንት አመት የፍቅር አጋሯ ጋር ስላላት ግንኙነት ትናገራለች፡፡ ቀላል ግን ጥልቅ የሆነ አገላለጽ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የምንኖር የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን የህይወታችን ቋሚ አካል የሆኑትን ችግሮች እና ፈተናዎች ማለፍ እንደምንችል ማሳያ ነው። የፍፁም ዘላቂና ፍቅር የተሞላበት የረጅም ጊዜ ግንኙነትም ህይወታችን በማይታበል ፍቅር የተሞላ እንደሆነ ያመላክታል፡፡

በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የፍቅር ግንኙነቶችን ወደምንዳስስበት የንስንስ አራተኛ እትም እንኳን በደህና መጡ። የተለያዩ ስርዓተ ጾታ አገላለጽ ተጠቃሚዎች፣ የሀይማኖት ተከታዮች፣ የብሔርና መደብ አባላት፣ እንዲሁም የገጠር ወይም ከተማ ነዋሪዎች የሆኑ ኢትዮጵያውያን የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ግንኙነቶችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች እንመለከታለን፡፡

አንዳንዶች በቲንደር የሞባይል መተግበሪያ በኩል ለጊዜያዊ ደስታ ተገናኝተው ለዘጠኝ ወራት የዘለቀ የአንድ ለአንድ ግንኙነት እንደመሰረቱት ሳራ እና ማህደር አብረው የወደፊት ህይወታቸውን እንዴት መገንባት እንደሚችሉ እያሰቡ ነው። በእርግጥ ሁላችንም የምንገናኝበት መንገድ ሊለያይ ይችላል ይሁንና የፍቅር ፍላጎታችን ሰው የመሆን አንዱ ማሳያ በመሆኑ የማህበረሰባችን ብዙ አባላት ታሪኮችን ያንፀባርቃል።

ታሪኮቻችን እንደ ማህበረሰባችን ብዙ ገጽታ ያላቸው እና ውስብስብ ናቸው። በከፊል ታሪኮቻችንን የሚያወሳስበው ሁሉም የተለመዱ ተብለው የሚታሰቡ አለመሆናቸው ነው። ታሪካቸውን ካካፈሉን ባለአምዶች አንዷ የሁለትዮሹ ጾታ አፍቃሪ ስትሆን ከባለቤቷ ጋር ስላላት ግንኙነት እና አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅ ስለምትከተላቸው መንገዶች ብዙ ትለናለች፡፡ “ስርአተጾታ እርስበርስ ባለን ትስስር ላይ ትልቅ ሚና ይጫወታል...” ስትል ጽፋለች። በታሪኳ አንድ ለአንድ ያልተወሰኑ ግንኙነቶች ምን ሊመስሉ ይችላሉ እና በጥንዶቹ መሀል ሊደረጉ የሚችሉ ስምምነቶችስ ምንድናቸው የሚለውን እንዳስሳለን፡፡

ከዚህ ቀደም በትዳር ውስጥ የነበረች የእስልምና እምነት ተከታይ፤ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ መሆኗን ስታውቅ ከባለቤቷ ጋር ብትለያይም አሁንም ማንነቷን ግልጽ ማውጣት ወይም ከሴቶች ጋር የፍቅር ግንኙነትን መፍጠር እንደከበዳት ታሪኳ ይነግረናል፡፡ “እስካሁን ከሴት ጋር የፍቅር ግንኙነትም ይሁን ወሲብ አድርጌ አላውቅም። ለዚህም ምክንያቱ ማህበረሰቡ እና ሃይማኖቴ ነው።” ትላለች፡፡ የምትፈልገውን ህይወት መኖር አለመቻሏ ማህበረሰቡ በእኛ ላይ የሚፈጥረውን ጫና የሚያንጸባርቅ ከመሆኑ በተጨማሪ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ራስን መቀበል አለመቻል በሕይወታችን ውስጥ የሚጫወተውን ሚና የምንመረምርበት ሌላ አቅጣጫ ይሰጣል።

ሌላዋ አምደኛችን “ሁሉም የዚህ ማህበረሰብ አባላት በተለይም ወንዳወንድነት* የሚታይብንን ሴቶች  *በቂ* የሆነ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ልምድ እንዲኖረን የሚጠብቅ በሚመስል የፍቅር ግንኙነት ዓለም ውስጥ እንዴት ልግባ?” ትለናለች፡፡

ከፍቅር ግንኙነታችን የምንጠብቀው ነገር ምንድን ነው? በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉ ግምቶች እና የተሳሳቱ አመለካከቶች በአጭር የወሲብ ብቻ ግንኙነቶች ወይም ዘላቂነት ያላቸው የፍቅር ግንኙነቶች ላይ እንዴት ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል? የመጀመሪያ ፍቅር፣ ግንኙነት እና መለያየት ምን ይመስላል? የፍቅር ግንኙነት ላለመጀመር ፍቃደኛ አለመሆንስ ምን ማለት ነው? በግንኙነታችን ውስጥ ከተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ማህበረሰብ ድጋፍ እንዳለን ይሰማናል? ዘላቂነት ባላቸው ግንኙነቶች ውስጥ ለመግባት እንዲሁም ለመቆየት የማያስችሉ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው? እነዚህን ጥያቄዎች በዚህ ጽሁፍ የምንዳስስ ይሆናል፡፡

በዚህ የንስንስ እትም ውስጥ ከምንመረምራቸው አንዳንድ ጉዳዮች የተወሰኑት ከላይ የተመለከትናቸው ናቸው፡፡ እንደማህበረሰብ በጋራ ልንወያይባቸው የሚገቡ ርእሶችን አንስተናል። በዚህ የንስንስ እትም ላይ ታሪካቸውን ያጋሩን አምደኞች ስለእነዚህ ጉዳዮች ለመወያየት እና የተመሳሳይ ጾታ ፍቅር ግንኙነት ገጽታን ለመዳሰስ ጊዜያቸውን ሳይሰስቱ ሰጥተውናል፡፡

በእትማችን መልሶችን ከመስጠት ይልቅ ብዙ ጥያቄዎችን እንጠይቃለን ይህም ወደራሳችን እና ውስብስብ ወደሆነው የህይወታችን ገጽታ መለስ ብለን ለመመልከት ይረዳናል ብለን እናምናለን።

እንደተለመደው በዚህ መጽሔት ዝግጅት ላይ የተሳተፉትን ሁሉ እናመሰግናለን፡፡ ታሪካቸውን እና የጥበብ ስራዎቻቸውን ላካፈሉን እና ለሚያነቡልን ሁሉ ምስጋናችን ከልብ ነው፡፡




በፍቅር ታዛ ስር

**ፍፁም እና ላይላ ለስምንት አመት በፍቅር አጋርነት አብረው የቆዩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ናቸው። ፍፁም ከንስንስ ጋር ባደረገችው ቆይታ ስለ ጣፋጭ፣ አስደሳች እና ፈታኝ የሆኑትን የግንኙነታቸውን ገፅታዎች እንዲህ ስትል ታጋራናለች፡፡ ቃለ መጠይቁ ለቦታ እና ግልጽነት ሲባል ማስተካከያዎች ተደርገውበታል፡፡**

> “
> **ክለብ ላይ ደሞ እንደገና ወዲያው ተገናኘን። ሙሉውን ሌሊት በርቀት ስንተያይ ነበር እና ጠራሗትና “መሳም እፈልጋለሁ አልኳት።”**
>
> **ፍፁም**

ንስንስ፡ እንዴት ተገናኛቹ?

ሌሎች ጓደኞች ላይላን ወደ እኔ ቤት ጠርተዋት ነው፡፡ ብዙም አላዋራኋትም፤ ላይላም ብዙ አላዋራችኝም። ከዛ በሌላ ጊዜ የሆነ ክለብ ውስጥ ሆነን ከሌሎች ጓደኞቿ ጋር እዛ መጣች እና እንደገና ተገናኘን። እዛ ስልክ ተቀያየርን።

ንስንስ፡ የመጀመሪያ ቀን ስትገናኙ ድፍረት ነው ያጣችሁት ወይስ በዛ መንገድ አልተያያችሁም?

ላይላ የመጀመሪያውን ቀን በመጥፎ ስሜት ታስታውሰዋለች። “የሆነ ቦታ አውቅሻለው?” አለችኝ። እኔ ደሞ አላወኳትምና መልስም አልሰጠኋትም። እሱ ነገር ደብሯት ነበረ።  ክለብ ላይ ደሞ እንደገና ወዲያው ተገናኘን። ሙሉውን ሌሊት በርቀት ስንተያይ ነበር እና ጠራሗትና “መሳም እፈልጋለሁ” አልኳት። በጣም ደንግጣ ነበር።  ከመገናኘታችን አንድ ቀን በፊት ልደቷ ነበር እና አንድ የሁለታችንም ጓደኛ የሆነች ልጅ በኔ ስልክ “መልካም ልደት” ብላ ልካላታለች። እና ክለብ ስንገናኝ እኔ እየወጣሁ ሳለ “እሺ ስልክሽን ስጪኝ” ስትለኝ “መልካም ልደት ተብሎ ተልኮልሻል” አልኳት። ከዛ ላይላም ፈልጋ አገኘችው እና ደወለችልኝ።

ንስንስ፡ ትውውቃችሁ እንዴት ወደ ፍቅር ግንኙነት ተቀየረ?

የተለያየ ባህል እና ታሪክ ያለን ሰዎች ነን። አንዳንድ ጊዜ የማንግባባት ነገር አለ ግን ስልካችንን ከተቀያየርን በኋላ በጣም ከባድ ሆኖ ነበር። ላይላ የነበረችበት ሁኔታ ከቤት መውጣት አይፈቀድላትም ነበር። አንዳንዴ “ሰፈር ነኝ” ብላኝ ሰፈር ሄጄ አምስት ደቂቃ ሳናወራ ከቤት ይደወልላትና “ግቢ” ትባላለች። የኔ ሰፈር ሩቅ ነው እና ተመልሼ ሰፈሬ ልደርስ ስል ትደውልና “አሁን ማውራት እንችላለን። ነይ።” ትለኛለች እና ተመልሼ እሄዳለው። ከቤት ሁላ በሺቲ ወጥታ መንገድ ላይ ልብስ ገዝተን ሁላ የቀየረችበት ጊዜ አለ። መውጣትም አትችልም እና እዚሁ አካባቢ ነኝ ለማለት በሺቲ በቤት ልብስ መውጣት አለባት። በጣም ትግስትሽን ነው የሚፈታተነው።

እንደዛ እያለ እየተግባባን መጣን። ያው ላይላ ላይ በቤተሰብ በኩል ጫና ነበረባት። መጨረሻ ላይ በቃ እናቷን አስተዋወቀችኝ እና “ፍፁም ነው የማገኛት ችግር የለም” አለቻቸው። እነሱ የሚፈሩት ተቃራኒ ፆታ እንዳትሄድ ስለነበረ እኔን ማስተዋወቅ ቀላል ነበር። በጓደኞቼም በኩል ብዙ ጫና ነበረ። እኔም ብዙ የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞች አሉኝ ስለኔ

የሚያውቁም የማያውቁም። ከጓደኞቼ ጋር ስቀላቅላት እና ወንዶች ጓደኞቼ ላይላን ሲፈልጓት እንዴት ብዬ ነው የማስቆማቸው ብዬ አስብ ነበር። የሷ መፍራት እና ሌሎች እንደዚህ አይነት ነገሮች ብዙ ነበሩ። እየተግባባንም ስለነበረ የሚባለውንና የማይባለውን ነገር ሁለታችንም አናውቀውም። እውነት ለመናገር ምንም ቀላል አልነበረም። ከባድ ጊዜ ነበር።

ንስንስ: QUEER/LGBT ከሆኑ ጓደኞች ጋር የተገናኛችሁባቸው ቀኖች ነበሩ?

እዛ ውስጥ አልነበሩም። የዛን ቀን ስትመጣ አንድ ጓደኛዬ ነበረ። ስለኔ ያውቃል እና አንዲት ልጅ ነበረች ስላልነገረችኝ  አላውቅም ግን ላይላን ኢንቫይት ያደረገቻት እሷ ናት። ጓደኛዬ ራሱ ምንም አያውቅም ብዬ ነው ያሳመንኳት። ትፈራለች እነደዚህ እነደዚህ ናቸው የሚባል ቦታ ላይ መሄድ በጣም ነው የምትፈራው። እና ልጁ ደሞ በጣም ይደግፈኝ እና ውድ ጓደኛዬ ስለነበረ ይሸፍንልኝ ነበር ስለዚህ ለተወሰነ ጊዜ አያውቅም አልኳት። እሱ ያውቃል ካልኳት እሱ ፊት ተቀምጣ ማውራት አትፈልግም ስለዚህ አያውቅም አልኳት ከዛ ከሆነ ጊዜ በኋላ ያውቃል አልኳት። ያው ለጥሩ ነገር እነደሆነ ስለገባት “በቃ ዋሸሽኝ አይደል” ምናምን ነው እንጂ ችግር አልነበረም እና ከሱም ጋር እንደውም አሁን ሁለቱ ናቸው ጓደኞች።

ንስንስ: አብራችሁ መሆናችሁን መግለፅ ባለመቻላችሁ አብሯችሁ ካሉ ጓደኞችሽ ምን ተፅእኖ ነበረው?

ብዙ ጓደኞች አሉኝ ግን ከሁሉም ዉስጥ ሁለቱ ብቻ ስለኔ ያውቃሉ። ሌሎቹ ግን አንዱ አንዱን ይጠራል እና አዲስም ስለሆነች ግሩፕ ላይ የተለመደ ነገር ነው። በዛ ላይ አንድ በጣም የምወደው ጓደኛ አለኝ እና ከሷ ጋር ሃይማኖታቸው አንድ አይነት ስለሆነ መቅረብ ፈልጎ ነበር። እኔ በግልፅ የምናገር ልጅ ነኝ እና የሚደብረኝን ይደብረኛል

> ከብዙ ነገር ጋር አልተጋጨባትም፤ ሁሌም ግልጽ በሆነ መንገድ ነው የምትጓዘው። “እንዴት አድርጌ ነው የማደርገው?” “እነደዚህ አይነት ሰዎች አሉ ወይ?” የሚለው ነገር ነው እንጂ የሚያስጨንቃት በደንብ ታውቀዋለች።
>
> ፍፁም

እላለው የማይደብረኝን አይደብርም ነው፤ ይሄ ሁኔታ ግን ፈተና ሆኖብኝ ነበር።

ንስንስ:  ለምን ያክል ጊዜ በዚህ ሁኔታ ቆያችሁ እና እናቷን ስትተዋወቂ ነገሩ ትንሽ ቀለለ?

ሶስት አራት ወር አካባቢ እንደዛ ነበረ። እና አዎ እናቷን ከተዋወቅኩ በኋላ ነገሮች እየቀለሉ መተዋል፤ ስራ አብረን መስራት ጀመርን። ብዙም ባይሆን ያው ተዋውቀን ስለነበረ ከዛ ለሷም ለቤተሰቧም የሚመቸው ምክንያት “ስራ እየሰራሁ ነው” የሚለው ነገር ነበር። ከዛ “ስራው ክፍለ ሃገር ነው” እያልን በቃ ማደር ጀመርን እና እዚህ ደረስን እልሻለው።

ንስንስ: አንቺ ከላይላ የበለጠ ነፃነት ነበረሽ እና የሷ ነፃነት አለመኖር ነገ ምን ያመጣል የሚለው አላሳሰበሽም?


አላሳሰበኝም። አንደኛ በጣም ነበር የወደድኳት። የመጀመሪያዬ አልነበረችም ለኔ፤ እኔ ግን ለሷ እስከነጭራሹ የመጀመሪያዋ ነበርኩ፤ ማለት እንደዚህ በቤተሰብ ምናምን የሚመጣላት እንጂ የፍቅር ጓደኛ ኖሯት አያውቅም። አንድ ልጅ ብቻ ነበር ለትንሽ ቀናት ያገኘችው። ከዛ ውጪ ለወንድም ለሴትም የመጀመሪያዋ ነኝ።

ንስንስ: በላይላ በኩል ከጭንቀቱ አንፃር ግንኙነቱን የመቀጠሉ ላይ ያላት አስተያየት ምን ነበር?

ሲመስለኝ ታውቀዋለች፤ ሁኔታዋን ታውቀዋለች። ከብዙ ነገር ጋር አልተጋጨባትም፤ ሁሌም ግልጽ በሆነ መንገድ ነው የምትጓዘው። “እንዴት አድርጌ ነው የማደርገው?” “እነደዚህ አይነት ሰዎች አሉ ወይ?” የሚለው ነገር ነው እንጂ የሚያስጨንቃት በደንብ ታውቀዋለች። በዛ ደረጃ ስለሆነ ምንም የሚያስጨንቃት አይመስለኝም።

ንስንስ: አብሮ ወደ መኖር የሄዳችሁት እንዴት ነው?

ወደቤት እንሄድና ልክ ልንደርስ ስንል አትገባም ቤት እንደገና ተመልሳ “እሺ ሻይ እንጠጣና” እንመለስ እንባባላለን፤ ከዛ ተመልሰን እናድራለን፤ እያልን እያልን በቃ እውነት ለመናገር አስበንበት አንድ ላይ ለመኖር ብለን ተጨንቀን ያደረግነው ነገር አልነበረም። በቃ መለያየት አልቻልንም። ከዛ ቤተሰቦቿ ቀስ እያሉ እየገባቸው መጣ ግን እስከ አሁን ድረስ በሷ በኩል ችግር አለ። አሁን ከ2-3 ቀን በፊት በሆነ በእህቷ በኩል “ባል



መጥቶልሻል” ተብላለች። እናቷ ግን ምን እያሰቡ እንደሆነ እኔ አላውቅም ፤ “አይ ተዋት ላይላ የወንድ ጓደኛ አላት።” ብለው ሁሉ መልስ ይሰጣሉ።

ከቤተሰቧቿ ጋር የልብ ጓደኛ ነኝ። ቤት እኛ ጋር ነው የሚያርፉት ምናምን። ሳስበው ደፍረው አልጠየቁም እኛም “ይጠይቁ” ብለን ዝም አልን እንጂ ትንሽ የሚያውቁ ይመስለኛል። አንዳንዴም ደግሞ አያውቁም እንዴ የሚያስብል ነገር ታያለሽ ግን የኔም ቤተሰብ ከሷ ቤተሰብ ጋር በጣም ይግባባሉ። ለምሳሌ እህቴ ስታገባ የሷ ቤተስቦች ሰርግ ላይ ነበሩ፤ በቃ ተቀላቅለናል ማለት ትችያለሽ።

> **የፍቅር ጓደኝነት ለሚወደው ሰው ያምራል፤ የፍቅር ጓደኝነት የምትወጂ ከሆነ ደግሞ መሆን ያለብሽ ነገሮች አሉ።**
>
> **ፍፁም**

ንስንስ: አብሮ መኖሩ እንዴት ነው?

በደንብ ይፈትናል በጣም ደስ የሚል ነገርም አለው። እንዴት እንደማስቀምጠው አላውቅም፤ ደስተኛ ነኝ ግን የሆኑ ነገሮች አብረሽ ስትኖሪ አንዳንዴ ይፈጠራል። እኔ ፈተና ብዬ የማስበው በሁለታችን መካከል የሚፈጠሩ ነገሮች ሳይሆን ከውጪ በሚመጣብን ነገር ነው። ቤት በጣም ነው የምንሳቀቀው። ለምሳሌ ሁለት መኝታ ቤት ነው ያለን። የሷ ወይም የኔ ቤተሰቦች ሲመጡ ያኛው ክፍል የሷ ነው ይሄኛው ክፍል የኔ ነው። ቤት ውስጥ አሁን የኔ ክፍል፣ የሷ ክፍል እየተባለ ነው የሚወራው። እንደዚህ ነገር አንዳንድ ጊዜ ነጻነትን ይጋፋል ፤ይጠፋል። ስለማያውቁ ዝም ብለው ይኖራሉ። ያኛው መኝታ ቤት አልተመቸኝም ብለው እኛ ጋር አንጥፈው አንድ ሳምንት ይተኛሉ። እሱ እሱ ነገር ነው በቃ የኛ ችግራችን እንጂ በመሃከላችን ያው ይፈጠራል እንደማንኛውም ሰው በግልፅ እንናገራለን። የደበረኝን፣ የደበራትን እና ሁሉንም እንነጋገራለን። እንደማንኛውም የሐበሻ ጥንድ ማለት ነው።

ንስንስ: የፍቅር ጓደኝነት ውስጥ መሆን ደስ የሚሉት ነገሮችስ ምንድናቸው?

ያው እኔ የማስበውን ልናገር። ሁልጊዜ የሆነ ሰው በህይወትሽ እንዳለ ታስቢያለሽ፥ ብቻሽን አይደለሽም፤ ብቻሽን አይደለሽም ብቻ ሳይሆን ደግሞ በጣም የምትወጂው በህይወትሽ ላይ ቦታ የምትሰጪው፣ ማጣት የማትፈልጊው ሰው ሁልጊዜ አጠገብሽ ነው። ታስቢያለሽ። አሁን ብቻዬን ስኖር እኔ በማንኛውም ሰአት መግባት እችላለው፤ በማንኛውም ሰአት መውጣት እችላለው ግን በማንኛውም ሰአት መግባቴን መውጣቴን ማንም ሰው አስቦ ቼክ አያደርግም። ግን ህይወትሽ ላይ የሆነ ሰው የሚጨነቅልሽ ሰው እንዳለ የሚወድሽ ሰው የሚያስብልሽ ሰው እንዳለ እያሰቡ መኖር በጣም ደስ የሚል ነገር ነው። ያኛውንም ኖሬዋለሁ ይሄኛውንም ኖሬዋለሁ። ስለዚህ የት ነሽ?

በላሽ ወይ ጠጣሽ ወይ? የምወዳቸው ነገሮች ናቸው። እኔም ላይላም የምናደርገው ነው። ለምወደው ሰው ዋጋ ኖሮኝ  እና አንድ ላይ መኖር ደስ ይለኛል። በጣም ደስ ይላል።

ንስንስ: የቀን በቀን ኑሮችሁ ከስራችሁም ዓንፃር ምን ይመስላል?

እኔ የተለያየ ስራ ነው ያለኝ። አንደኛው ስራ ላይ ከላይላ ጋር ነው አብረን የምንሰራው፥ ባብዛኛው ላይላ ነች የምትቆጣጠረው እና ቤቱን ላይላ ናት የምታስተዳድረው። ምንም ብዙ የምለው ነገር የለም ቤት ላይም አስተያየት አልሰጥም ግን በደንብ ታስተዳድረዋለች።

ንስንስ: ፍቅርና ስራ አብሮ መሆኑ ችግሮች ይኖሩታል?

አሁን ለምሳሌ ቢዝነስ ላይ ሆነሽ ከሰራተኛ ጋር ስትሰሪ ማንኛውንም ውሳኔ ብቻሽን ማሳለፍ ትችያለሽ፥ ከላይላ ጋር መስራት ከመጀመሬ በፊት ውሳኔዎቼ ማንንም ሳላማክር በግሌ ትክክል ናቸው ብዬ ያሰብኩባቸው ነበሩ። እንዴት እንደዚህ ደንበኛ ታናግሪያለሽ ልል እችላለው። የኔ ስምምነት ላይ ገብተሽ እንዴት ይህን ሐሳብ ሰጠሽ? ይሄን ዋጋ ለምን ሰጠሽ? እንጣላለን እና እንጨቃጨቃለን። ግን ከግል ህይወታችን ጋራ አናገናኘውም። ቢቃ እሱን ነው የተማርነው። እኔም ከሆነ ጊዜ በኋላ የገባኝ ነገር እሱ ነው። ወይ ስራ ላይ ወይ በሆነ ነገር ብንጋጭ የግል በሆነ ግንኙነታችን ላይ አናመጣውም። ተናድጄ የሆነ ሰዓት ልቆይ እችላለው፥ ተናዳ የሆነ ሰዓት ልትቆይ ትችላልች ግን ወደ ስሜቷ ስትመለስ እኔም ስመለስ ፍቅር እንዳለን አንረሳም፡፡

ንስንስ: በፍቅር ግንኙነታችሁ ውስጥ ምን ችግር ያጋጥማችኋል?

ብዙ ችግር። አንዳንድ ጊዜ ላይላ ምን ጠቅሚታል ይመስለኛል በባህሏም ከሀይማኖቷም አንፃር ያንን ነገር የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪም ብትሆኚ የምታሳይው ነገር የለም እና ከጓደኞች ጋር ተሰብስበን

“ . . . ህይወትሽ ላይ የሆነ ሰው የሚጨነቅልሽ ሰው አንዳለ የሚወድሽ ሰው የሚያስብልሽ ሰው አንዳለ አያሰቡ መኖር በጣም ደስ የሚል ነገር ነው::

ፍፁም

ብታይን ምናልባት እዛና እዚህ ልንቀመጥ እንችላለን ግን ሁልጊዜ ያለውን ነገር በዓይናችን እናወራለን እንግባባለን። አጠገቤም ልትቀመጥ ትችላለች ምንም አይረብሸኝም ግን እናርገው ብንል የምንወደው ነገር ነው ሁለታችንም፤ ለሁሉም ሰው የኔ እንደሆነች መግለፅ እፈልጋለሁ ላይላም እንደዛው። ይሄንን ፈልገን ራሱ 3ኛ ወይም 4ኛ አመታችንን ባንኮክ ነው ያከበርነው። በነፃነት ብቻችንን አስከፍተን የልደት ዘፈን ለምወደው ሰው ብለን አረግነው። እና ከባድ ነው ያው የምልሽ ተፅእኖ ቤት ውስጥም ይመጣል።

የሷ ወይም የኔ ቤተሰቦች ሲመጡ እነደጓደኞች ነን።

ንስንስ: ይሄንን በህበረተሰቡ ያለውን ጫናን በምን ምንገድ ነው የምታስተናግዱት ወይም የምታቀሉት?

ነፃ የምንሆንበት ጊዜ ብዙ አለን፤ አብረንም ስለምንኖር ቤት ውስጥ ጓደኛችንም ያው የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ስለሆነች አብዛኛው ጊዜ ነፃ ነን። እነሱ ጋርም ነፃ መሆን ደስ ይለናል ግን ለምን እንደሆነ አላውቅም ረብሾኝ አያውቅም። እኔንጃ፣ ላይላ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ቤታችን ሲኖሩ ደስ ይላታል እንዲኖሩም ትፈልጋለች። ፓርቲ ስናረግ ሁላችንም አንድ አይነት ነን በጣም ደስ ይላታል፤ እኔ ግን ምንም አይሰማኝም። ማንም ቢሆን ማንም ምንም አይመስለኝም። ላይላ ግን እኛን የሚመስሉ ሰዎች በጣም ትወዳለች። በፊት ለመዝናናት ስንወጣ እንደውም እነደዚህ ሰዎች ያሉበት ቦታ የማትሳቀቂበት ቦታ ነው፤ ሲንግልም ሆነሽ እራስሽን ስትገልጪ መሳቀቅ የለብሽም። እነደዚህ አይነት ቦታ ላይ ስትሆኚ ደስ ይልሻል። እዛ ስሄድ ደስ ይላል፤ ላይላም የምትወደው ነገር ነው።

ሁለቱም ባላንስ ቢሆን አሪፍ ነው። የውጪውን ብቻ የምትፈልጊ ከሆነ እሱን ስታጪ ስሜትሽ ሊጎዳ ይችላል። መጀመሪያ የውስጥ የሆነው ነገር በጣም ከጠነከረ እኔ ቢቃ አለባበሴም ምናምንም አይታየኝም፤ ምንም አይነት ኮሜንት ቢሰጡ ምንም አይመስለኝም። መሆን የምፈልገውን ነገር ብዙ ጊዜ አልቆጥብም፤ ላይላ እንደውም ትሳቀቃለች። ስለዚህ ብዙ ጊዜ ላይላ አንዳንድ ቦታዎች መሄድ ትፈልጋለች ፤ እኛን የሚመስሉ ሰዎች ያሉበት። ቢመጡም ያው ስርዓታችንን ይዘን ነው የምንቀመጠው፤ እኛን የሚመስሉ ቢሆኑም።

ንስንስ: የፍቅር ጓደኝነት ውስጥ እነደሆናቹ ምን ያህል ሰው ያውቃል?

እስከማውቅው ድረስ ብቻዋን ላይላ የነገረቻቸው ሰዎች የሉም። እንደ

ፍቅረኞች ግን በኔ፣ በጓደኞቻችን እና በኔ ጓደኞች ምክንያት ስንሄድ ምናምን ብዙ የሚያውቁ ሰዎች አሉ። በተለይ በኩዌር ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ጓደኞቻችን 50 የሚሆኑ ሰዎች ያውቃሉ እንገናኛለንም።

ንስንስ: በነፃነት እንደ ፍቅረኛ እራሳችሁን መሆን የምትችሉበት ቦታዎች ለአንቺ ወሳኝ ነው?

እነደሱ ቦታዎች ስንሄድ ደስ ይለናል። እኔ ግን እንደ ፍቅረኛ መሆናችንን ቢታወቅ ባይታወቅ እኔ ከኔ ጋር እስከሆነች ደረስ ሌላው ምንም አያሳስበኝም። እውነቱን ለመናገር ያለሷ ብዙ ነገሮችን መስራት አልችልም። ያለሷ መውጣት መዝናናት እና ያለሷ ቤት ውስጥ መሆን ብዙም ምቾት አይሰጠኝም። የት እነደሆነች እና ምን እያደረገች እነደሆነ ማወቅ አለብኝ እና ላይላ እስካለች ድረስ ሌላው ብዙም አያስጨንቀኝም።

ንስንስ: አንቺ በ8 አመት ያካበትሻቸው የህይወት ተሞክሮዎች በምን ይገለፃሉ? የረጅም የፍቅር ጓደኝነት ውስጥ ለመቆየት ቁልፉ ምንደነው?

ራስሽን ማገኘት ነው እዛ ውስጥ፤ እራስሽን ሆነሽ መገኘት ነው። መሬት ያልወረዱ ነገሮችን አለማውራት ምክንያቱም የፍቅር ጓደኝነት ውስጥ ስለሆንሽ ነገም እነዛ ቀኖች ይመጣሉ ያን ነገር መሆን የማትችይበት ስለዚህ እራስሽን ሁኚ ቢቃ። አሪፍም ይሁን ጥሩ ያልሆነ ማንነት ራስሽን ሁኚ ግን አሪፍ ካልሆነ ተስማምተሽ ለመቀየር መሞከር።

አሁን እኔ በጣም የተለየሁ ሰው ነበርኩ በፊት የትም አትይገርኝም ነበር፤ በጣም ለራሴ ቦታ ነበረኝ እና የኔ የምላቸው አራት መዐዘን ያደረኩባቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ። እነሱ ነገሮች የፍቅር ጓደኝነት ላይ የሚሰሩ አይመስለኝም ምክንያቱም ሁለታችንም ጥሩ ሰዎች ነን እና ነጻነት ሊሰጠን ይገባል። አንዳችን አንዳችንን አሳንሰን ማየት በጭራሽ አንችልም። ይቺ አለም በምትለካው መስፈርት አንቺ እኔን እኔ አንቺን አሳንሰን

> **“**
>
> **ላይላ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ቤታችን ሲኖሩ ደስ ይላታል እንዲኖሩም ትፈልጋለች። ፓርቲ ስናረግ ሁላችንም አንድ አይነት ነን በጣም ደስ ይላታል፤ እኔ ግን ምንም አይሰማኝም። ማንም ቢሆን ማንም ምንም አይመስለኝም። ላይላ ግን እኛን የሚመስሉ ሰዎች በጣም ትወዳለች።**
>
> **ፍፁም**

ማየት አንችልም። ምክኒያቱም እኔ ለራሴ አለኝ እኔ ብዬ የማስባት እና የማከብራት ልጅ አለች ላይላም እንደዛው።

አሁን እኔ በፊት የነበርኩት ቀስ በቀስ ልክ እንዳልሆነ እየተየኝ ሄደ እና በጣም ብልህ ናት እንዴት አድርጋ እንዴት እንደምታደርገኝ ታውቀዋለች ደግሞም ወድጃታለው ትሰማኛለች እናም እሰማታለው። የፍቅር ጓደኝነት የምታስቢ ከሆነ ያቺን ነገር መተው ማድረግ አለብሽ፤ እሱን ነው እምለው እንጂ ቢቃ ራስሽን መሆን ምንም ሌላ ነገር አያስፈልገውም።

ንስንስ: ግጭት እና አለመግባባት ሲኖር በምን መንገድ ይፈታል?

ሰው መሃከላችን ገብቶብን አያውቅም ግን ብዙ አለመግባባቶች ተፈጥረው ያውቃሉ። ተጨቃጭቀን ባንዘጋውም ክፍት እንተወዋለን እኔም ወደምሄድበት ላይላም የምትሄድበት ያን ሰአት ላይ ሁለታችንም አስበን ስንመለስ ቀዝቅዘን እንመለሳለን። እና አንዳንዱ ሳንግባባበት እዛው ተከድኖ ይቀመጣል፥ የግድ መፈታት አለበት ማለት አይደለም። አንዳንዱ ደሞ ትክክል ነሽ ተባብለን የምናልፍበት ነገሮች አሉ። ደሞ ሳይፈቱ ሲቆሰቆሱ ስንጠላባቸው እየተገደሉ ሲቆሰቆሱ እየተጣላን ምንም ችግር የለውም።

እኔ ብዙም ጭንቀት አይመቸኝም ነገር ይዞ መቆየት አልወድም እንደዛ ትረዳዋለች ይመስለኛል። አንዳንዴም ያው ይውጣልሽ ትለኛለች ይወጣልኛል። ብዙም ጓደኛም ሆነናል ይመስለኛል ተዋውቀናልም። ጓደኛችን ይገርማታል ምንም ሳናወራ የሆነ ውሳኔ ላይ አብረን እንደርሳለን እነደዚህ ተቀምጠን ማለት ነው። እነደዛም ስለሆነ አንዳንዴ እንስቃለን ተጨቃጭቀን አንቺ እንደዚህ አስበሽ ነው አንቺ እንዲህ ነበር ብለን እናልፈዋለን።

የፍቅር ጓደኝነት ለሚወደው ሰው ያምራል፤ የፍቅር ጓደኝነት የምትወጂ ከሆነ ደግሞ መሆን ያለብሽ ነገሮች አሉ።


ንስንስ: ከላይላ በፊት የነበሩሽ የፍቅር ግንኙነቶች እንዴት ነበሩ?

ከዚህ በፊት የፍቅር ጓደኝነት ውስጥ ነበርኩኝ እና ቀላል አልነበረም። እኔ ራሴ ይገርመኛል። እኔ ነኝ ጊዜ ሲያልፍ የተቀየርኩት ወይስ እነዛን ልጆች ተመልሼ ይቅርታ ማለት አለብኝ? በጣም ከባድ ሰው ነበረኩኝ። አልሰማም። አሁን እኮ እሰማለው። የት ነሽ ተብዬ መጠየቅ እንኳን አልፈልግም። ስንት ሰአት ነው የምትመጪው ካልሺኝ ስመጣ ታገኚኛለሽ ነበር የምለው። አሁን ስንት ሰአት ትመጫለሽ ስባል ስንት ሰአት ልምጣ ነው የምለው።

እሷ ደስታዬ ሆነች እውነቱን ለመናገር ከከፋት ይከፋኛል፤ ጠዋት ተነስተን ከደበራት ላይላ እንዳይደብራት ምን ማድረግ አለብኝ ነው ስራዬ የሚሆነው፤ ለማሳቅ እሞከራለው። እንደዚህ አይነት ሰው አልነበረኩም። በፊት በራሴ ጥፋት ተናገርሽኝ ወይም የሆነ ነገር አልሽኝ ብዬ  ጦርነት ነው የምፈጥረው። አሁን ግን በቃ ፊቷን ነው የማየው፤ ደብሯታል አልደበራትም? ከዛ ወደኋላ መለስ ብዬ ምን ብያት ይሆን? ትላንት እራሱ እየነግረኳት ነበረ አንቺ ደስታዬ ሆነሻል ብዬ። ከፍቷት ማየት አልፈልግም። የትኛውም ድረስ እሄዳለው ላይላ እንዳይከፋት። በቃ ላይላም ብዙ ከፍላለች፤ ቀላል አይደለም እናትሽን ማስከፋት ቀላል ነገር አይደለም። ለኔ ብላ ሁሉንም ነገር ትታለች። ቤተሰቦቿን የማትሰማማበት ደረጃ ማለት እኔን አሰቀደመችኝ። እና ከፍቷት ማየት አልፈልግም በተለይ በኔ ምክኒያት የሆነ ነገር አድርጌ ከፍቷት ማየት አልፈልግም ሳይሆን በቃ በጣም ደስተኛ እንድትሆን ነው የምፈልገው። ህልሜ ነው ብልሽ ይገርምሻል። የምሬን ነው።

ንስንስ: በግልፅ እራሳችሁን ትገልፃላችሁ?

እናደርጋለን። እኔ አንዳንዴ እንደውም ትንሽ ቁጡ ነኝ። እናወራለን። እነግራታለሁ። እዚህ አሁን ያልኩሽን



> የት ነሽ ተብዬ መጠየቅ እንኳን አልፈልግም። ስንት ሰአት ነው የምትመጪው ካልሺኝ ስመጣ ታገኚኛለሽ ነበር የምለው። አሁን ስንት ሰአት ትመጫለሽ ስባል ስንት ሰአት ልምጣ ነው የምለው።
>
> ፍፁም

> አንደአንድ አድርገው ይቆጥሩናል። አናቴ ደውላ አሁን "ሽሮ የለሽም ወይ በርበሬ የለሽም ወይ?" አትለኝም፥ "ሽሮ ጨረሳችሁ አለቀባችሁ? በርበሬ አለቀባችሁ? "እኔንጃ ማማ" ካልኳት፥ "ጠይቂያት አስቲ ላይላን" ትለኛለች።

**ፍፁም**

ነገሮች እነግራታለው። ላይላ እንደዚህ በግልፅ ባትልም ትላለች።

መብላቴና አለመብላቴ ያሳስባታል፤ ቤቱን እንዴት እንምትገለብጠው፤ እናቴ ብያት። ጓደኞችን በጣም ይገርመዋል "ግድ የላትም እኮ ማንም ኖረ አልኖረ ላይላን የሚያሳስባት ያንቺ መብላት ያንቺ ምቾተኛ መሆን ነው" ይላል ። ምንም አይመስላትም። አሁን እነደዚህ እያልኩሽ እህቶች፣ ወንድሞቻችን እንደዛ እያስጨነቁን እነሱ ሁሉ ተሰብስበው እኔ የደበረኝ ከመሰላት ወይ የሆነ ነገር ፈልጌ ማድረግ ያቃተኝ ከመሰላት ሁሉንም ትረሳዋለች። አንዳንድ ጊዜ ይገርመኛል። እና ተዘጋጅታለች ምንም አይነት ችግር ውስጥ ለመግባት እኔም እነደዛው። ምንም ቢሆን ላይላ ሁሌም መጀመሪያ ነች። እና ይሄ የመጣው ብዙ ክፉና ጥሩ የሆኑ ነገሮችን ስታዪ ነው። እዚጋ የደረስነው ብዙ መጥፎ ቀኖች አልፈው ነው። እነዛን ሁሉንም አንድ ላይ ስታልፊያቸው እዚህ ጋር ትመጫለሽ።

አሁን የኛ ችግር ልጅ ነው። እንዴት ነው የምናደርገው፥ ላይላ በጣም ትፈልጋለች፣ እኔም እፈልጋለሁ ግን ያሉት ነገሮች ቢቀርብኝስ እላለሁ? ምንም ነገር ቢጠበቅብን ልጅ እንድናገኝ ምንም ነገር የምናደርግ ይመስለኛል። ደስታችን ይመስለኛል በተለይ ላይላ በጣም መውለድ ትፈልጋለች፥ ይሄ ነገር ሊያልፈኝ ይሆን ሳላደርገው፥ ለሷ ባልላትም ይረብሸኛል። ጓደኞቿ ሲያገቡ እና ሲወልዱ ምናምን ምንም አልላትም ግን ምንም አይነት አማራጭ ብታመጣ ተቀባይ ነኝ።

ከእህቶቿ ልጆች ጋር ስትጫወት ሳይ መስጠት የማልችለው ነገር ስለሆነ ይረብሸኛል። ከዛ ውጪ ሰላም ነን። አንዳንዴ በዚህ ምክንያት ራሱ ያለንን ነገር ሽጠን እንሂድ እንዴ እላለሁ። ከዛ ደግሞ ታስቢዋለሽ፥ እንዴት ነው የሚሆነው መቼ ነው የሚሆነው ከዛ ይሄን ጥለን ሄደን ደግሞ ይሆን ይሆን ወይ ቢከብደንስ እንላለን፡፡ የማይመለስ ጥያቄ ነው፡፡ ሁሉንም ነገር አስበነው መመለስ አቀተን። ብናሳድግ ብናደርግ ሁለታችንም የልጁ ህይወት አካል መሆን እንፈልጋለን እዚሁ ሀገር ግን አይሆንም። ለቤተሰባችን ምን ልንል ነው? አይሆንም። የሷም ቤተሰብ ከትዳር በፊት ልጅ ይከብዳቸዋል። ግን ከኢትዮጵያ ውጪ ብናረገው በማይጎዳቸው መልኩ ዜናውን ይሰሙታል።

አንዳንዴ ማንም እንደማያስታርቀን ስለምናውቅ ሁለታችንም ዝግጁ ነን ለመታረቅ። ሁለታችንም ደብሮን ቤት ውስጥ ማሳለፍ ስለማንፈልግ የሚያስታርቅ ስለሌለ ተግባብተሽ ትኖሪያለሽ። እውነቱን ለመናገር አብረን መኖራችን ለሷም ቤተሰቦች ለኔም ቤተሰብ ብዙ ከባድ ነገር አይደለም። በፊት ነበር የሷ ቤተሰቦች የሚጠይቁት አሁን ግን "ወደቤት ነይ" ሲሏት "ማንም እኮ ቤት የለም። ፍፁም የለችም።" ስትላቸው ይተዋት እና "ስትመጣ ንገሪኝ" ይሏታል።

ላይላ ካልቻለች እህቶቿ ከመጡ እኔ ነኝ ሄጄ የማመጣቸው። የሷ እህት መጥታ እኔ ከሌለሁ ቤት በጣም ይደብራታል፥ የእኔ እህት ደግሞ ስትመጣ ላይላ ከሌለች ይደብራታል። እንደዛ ነው የምንኖረው፥ ወንድሜ ቤት ሲመጣ የሚፈልገውን ነገር ላይላን እንጂ እኔን አይደለም የሚጠይቀው። የሷም ቤተሰቦች እንደዛ። እንደአንድ አድርገው ይቆጥሩናል።

እናቴ ደውላ አሁን "ሽሮ የለሽም ወይ በርበሬ የለሽም ወይ?" አትለኝም፥ "ሽሮ ጨረሳችሁ አለቀባችሁ? በርበሬ አለቀባችሁ?"

"እኔንጃ ማማ" ካልኳት፥ "ላይላን ጠይቂያት እስቲ" ትለኛለች።

የሷም እናት ደውለው ምሳ በላች ወይ ካልበላች ልላክላት ብለው ይልኩልኛል። እኔ እውነት ለመናገር ልጅ መውለድ አለመቻል ውጪ ምንም ችግር የለንም። አንዳንድ ግዜ ግን የሷ ቤተሰቦች "ባል አግኝተናል" ምናምን ይላሉ። ያው ተሳስቀን እናልፈዋለን። ደስ ብሎን ነው የምንኖረው።



“

ከፍቷት ማየት አልፈልግም በተለይ በኔ ምክኒያት የሆነ ነገር አድርጌ ከፍቷት ማየት አልፈልግም ሳይሆን በቃ በጣም ደስተኛ እንድትሆን ነው የምፈልገው። ህልሚ ነው ብልሽ ይገርምሻል። የምሬን ነው።

ፍፁም



“እንደዚህ እንቆያለን ብዬ አስቤ አላውቅም። አንዳችን ለአንዳችን ያለንን ነገር በጣም ወደድነው። እናም በደንብ እየተዋወቅን ስንመጣ ያለን ነገር ወደ ፍቅር መቀየር ጀመረ ግን አስበንበት አልነበረም።”

- ማህደር

# ለፍቅራችን ህያልነት

በአንድ እሁድ ከሰአት ንስንስ ለማህደር እና ሳራ ስትደውል ሳራ ለቃለመጠይቁ ስለዘገዩ ይቅርታ በመጠየቅ “ማህደር ልብስ እያጠበች ነው” ስትል የቤተሰብ ህይወታቸውን በሚያመላክት መልኩ ትነግራታለች። ለዘጠኝ ወራት አብረው የቆዩት ማህደር እና ሳራ ፈታኝ ቢሆንም የፍቅር ግንኙነት ብዙ ስራ የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት የተረጋጋ ህይወት ሊኖራቸው ችሏል፡፡

“ብዙ ሰዎች የፍቅር ግንኙነትን በተፈጥሮ ቀላል አድርገው ያስቡታል። እውነቱ ግን የሁለቱን ሰዎች እሴቶች እና ፍላጎት አብሮ የሚሄድ መሆኑን ለመረዳት መግባባትን ይጠይቃል፡፡’ ስትል ማህደር ትናገራለች፡፡ “በጣም አስፈላጊ በሆኑት ነገሮች ላይ ብቻ

> “
> **ከስራ አስክትወጣ ጠበቅኩ አና ቀጥታ ወደ ቤቷ ሄድኩ። ከዛን ቀን ጀምሮ አልተለያየንም። በጣም በፍቅር የተሞላ አለት ነበረ።**
>
> **ሳራ**

ለማተኮር ግንኙነታችን ላይ በደንብ እንሰራለን። ሁለታችንም ያለንን ነገር ማጣት አለመፈለጋችን እና ጊዜያችንንና አቅማችንን አውጥተን መስራታችን እስከዚህ ጊዜ እንድንቆይ ረድቶናል።”

ሳራ እና ማህደር “ቲንደር” በተባለ የሞባይል መተግበሪያ በኩል የተዋወቁ ሲሆን ሁለቱም መጀመሪያ ላይ ቁም ነገር ያለው ግንኙነት አይፈልጉም ነበር። ወዲያውኑ ማች ቢያደርጉም ማህደር የመተግበሪያው አዘውታሪ ተጠቃሚ ባለመሆኗ ከሳራ ጋር በመተግበሪያው በኩል መገናኘቷን ለማወቅ ጊዜ ወስዶባታል፡፡

ማህደር ከሳራ ጋር በመተግበሪያው ካወራች በኋላ የቴሌግራም አካውንት ተለዋወጠው ከሁለት ቀን በኋላ ለመገናኘት ወሰኑ። ማህደር መጀመሪያ ሲገናኙ ፈርታ እንደነበር ሳራ ታስታውሳለች።

“እኔ ነበርኩ እንድንገናኝ ሃሳቡን ያመጣሁት” ትላለች ሳራ “እሷ ፈርታ ነበር። ከስራ እስክትወጣ ጠበቅኩ እና ቀጥታ ወደ ቤቷ ሄድኩ። ከዛን ቀን ጀምሮ አልተለያየንም፡፡ በጣም በፍቅር የተሞላ እለት ነበረ። እኔ ፒዛ ገዛሁ እሷ ደግሞ ወይን አመጣች፣ ጉዞአችን የጀመረው ከዛ ነው፡፡”

መጀመሪያ ሁለቱም ቀጣይነት ያለው የፍቅር ግንኙነት ያልፈለጉ ቢሆንም በኋላ ላይ ግን ቋሚ ወደሆነና እና አንድ ለአንድ የተወሰነ ግንኙነት መሆኑ ደስ ብሏቸዋል። ቶሎ ቶሎ መገናኘታቸው እና ሲገናኙ የሚያወሯቸው ነገሮች ትውውቃቸው እንዲጠነከር ረድቷቸዋል፡፡

ማህደር ስለግንኙነታቸው ስታወራ “እንደዚህ እንቆያለን ብዬ አስቤ አላውቅም። አንዳችን ለአንዳችን ያለንን ነገር በጣም ወደድነው፡፡ እናም በደንብ እየተዋወቅን ስንመጣ ያለን ነገር ወደ ፍቅር መቀየር ጀመረ ግን አስበንበት አልነበረም።”

የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ማህበረሰቡ በብዛት ትንሽ ቢሆንም ሳራ እና ማህደር ከዚህ በፊት ተገናኝተው አያውቁም ነበር። ሳራ በማህበረሰቡ ውስጥ ተሳትፎ የምታደርግ ቢሆንም ማህደር በሳራ በኩል ጓደኞቿን እስክትተዋወቅ ድረስ ብዙም ተሳትፎ አልነበራትም፡፡

ሳራ ማህደርን ‘ደስ የምትል’ ስትል ታስታውሳታለች። በተከታታይ የሚያደርጓቸው ጥልቅ ውይይቶች በይበልጥ እንዲገናኙ እንድትፈልግ አደረጋት፡፡ “የፍቅር ግንኙነታችን እየጠነከረ እንዲመጣ ያረገው አስበን ያደረግናቸው ውሳኔዎች ናቸው። ለመገናኘት እና ብዙ ጊዜ አብረን ለማሳለፍ እንጥራለን፡፡ የሳምንቱን መጨረሻ ቀናት አብረን እናሳልፋለን፡፡ እንደዛም ሆኖ ግን የየራሳችንን ጊዜ እና ስራችንን እናከብራለን።”

ዘጠኝ ወር ሳይሆን ዘጠኝ አመት የቆዩ ያህል እንደሚሰማት ሳራ ትናገራለች። “ከፍቅር ጋር የሚመጣ መተሳሰብ እና መዋደድ ብዙ ነው።”

በኢትዮጵያ ካለው የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ተቃውሞ አንጻር ይህ ህይወት ከባድ ነው። ሳራ እና ማህደር አብረው ለመኖር አስበው ነበር ግን ማህደር ከእናቷ ጋር ያላት ቁርኝት ይህንን ከባድ አድርጎታል። ብዙ ምሽቶችን አንዳቸው ሌላኛቸው ቤት በማደር ቢያሳልፉም አብሮ መኖር ግን ከባድ ሆኖባቸዋል። ማህደር እናቴ ምን ትለኛለች የሚል ፍርሀቷ ይዟታል፡፡ ቤተሰቧ በጣም ወግ አጥባቂ በመሆኑ እናቷ መቼ አግብታ መውለድ እንዳሰበች በተደጋጋሚ ትጠይቃታለች፡ወደ ሀያዎቹ አጋማሽ ስትጠጋ የተለመደውን በኢትዮጵያ ማህበረሰብ የሚጠበቀውን የትዳር ህይወት መጀመር እንዳለባት ታስባለች፡፡

“ይሄ ነው ቢቃ ዋና የሚያከራክረን ነገር። ቤተሰቦቼን ቀስ በቀስ ከሳራ ጋር መሆኔን መቀበል እንዲችሉ ለማሳመን ጊዜ እንድትሰጠኝ ጠይቄያታለሁ።” ስትል ትናገራለች ማህደር “እናቴን በድንገት ከህይወቴ ማስወጣት አልችልም። ጊዜ የሚወስድ ነገር ነው”

የማህደር እናት ሳራ የማህደር ጓደኛ ነች ብላ የምታስብ ሲሆን ምንም እንኳን ሳራ ፍቅረኛ እንደሆኑ እንዲታወቅ ብትፈልግም በቤተሰቡ ፊት ጓደኛ ብቻ መስላ ትቀርባለች፡፡

የሳራ ቤተሰብ ከዚህ በጣም የተለየ ነው። ከልጅነቷ ጀምሮ ብቻዋን ስለኖረች ከቤተሰቦቿ ጋር ብዙም ቅርበት የላትም፡ እህቷ ስለተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነቷ እንደምታውቅ ትጠረጥራለች፡፡ ይሁንና የቤተሰቦቿ ማወቅ አያሳስባትም፡፡ “ቢያውቁ ይናደዳሉ ግን ከዛ ውጪ ምንም የማጣው ነገር የለም። የምወስናቸው ነገሮች ላይም የሚያመጣው ለውጥ የለም።” ትላለች ሳራ።

በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ማህበረሰብ ውስጥ እንደፍቅረኛ መታየታቸው እናም የሚያገኙት ድጋፍ ፍቅራቸውን ከሚያጠናክሩላቸው ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ሳራ “እሷ የኔ ነች” ማለት እና እጅ ለእጅ ተያይዞ ደህንነታቸው በሚጠበቅባቸው ቦታዎች ፍቅር ማሳየታቸው ምቾት እና ደስታ እንደሚሰጣቸው ትናገራለች።

ሳራ “ብዙውን ጊዜ ደስተኛ ነኝ።” ስትል እየሳቀች ትናገራለች “የማስታውሰው ያዘንኩበት ጊዜ ፀጉሯን




የተቆረጠች ጊዜ ነው። በጣም እወደው ነበር ግን ከስራ ጋር ተደራርቦ መንከባከብ ስላቃታት ቆረጠችው።"

ማህደርም በጣም ትልቅ የሆኑ የፍቅር ግንኙነት ችግሮችን ማስወገድ የቻሉት ግልፅ ሆነው ስለሚያወሩ እንደሆነ ትገልጻለች፡፡ በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ማህበረሰብ ውስጥ በአብዛኛው ግንኙነት ጠብቆ የማይቆየው ሰዎች ለማውራት በግልጽ ለመነጋገር ፈቃደኛ ስላልሆኑ ነው ብላ ታስባለች።

ማህደር ከሳራ በፊት ሌላ አንድ የፍቅር ግንኙነት ብቻ የነበራት ሲሆን ያኛው የፍቅር ግንኙነት ያልሰራበት ምክንያት መግባባት እና መደጋገፍ ስላልቻሉ እና የነበራት መረዳት ጤናማ ባለመሆኑ ነው ትላለች፡፡  ሳራ ፍቅር ምን እንደሆነ ስላሳየቻት ታመሰግናታለች። ለፍቅር ግንኙነት አስፈላጊ እንደሆነ ስለምታምን የማህበረሰቡ ድጋፍ ቢኖረኝ ብላም ትመኛለች። የማህደር ቤተሰቦችም ሆኑ ጓደኞች የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ እንደሆነችና ከሳራ ጋር ግንኙነት እንዳላት አያውቁም። በዚህም ምክንያት ስለችግሮቿ የምታዋራው ሰው ማግኘት ለሷ ከባድ ነው፡፡

''ብዙ የፍቅር ግንኙነቶች የማይቆዩበት አንዱ ምክንያት ይሄ ነው'' ስትል ትናገራለች ''ሁለታችንም ጋር ችግር ቢኖር የሚያስታርቅ የውጪ ሰው የለም። እና የውጪ ተፅዕኖ አለ። እሱን ለመቋቋም ደግሞ ጠንካራ መሰረት ያስፈልጋል።'

ሳራ ብዙ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች የሌሎችን የፍቅር ግንኙነቶች አያከብሩም ብላ ታስባለች። እናም ይህ አለመተሳሰብ አንዱ እነዚህ ግንኙነቶች እንዲዘልቁ የሚረዳ ማህበረሰብ በዙሪያቸው እንዳይኖር ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡ ከዚህ በፊት የነበራት አንድ ግንኙነት የፈረሰው በግልጽነት መነጋገር ባለመቻላቸው እንደሆነ ትናገራለች፡፡ ሌላው ደግሞ ከማህበረሰቡ ምንም አይነት ድጋፉ አለመኖሩ ነው፡፡ የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪዎች በማህበረሰቡ የተለመዱት እንደአስታራቂ ሽማግሌ ያሉ መንገዶች በመኖራቸው የሚታረቁበት አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል፡፡

"በእኔ ተሞክሮ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጓደኞቼ የኔን የፍቅር ግንኙነት እንደማይደግፉት አይቻለሁ። እንደዚህ አይነት አስተሳሰብ እንዴት መቀየር እንዳለብን ማወቅ ይኖርብናል። ብዙ መስራት ያለብን ስራ አለ። በማህበረሰባችን ውስጥ ብዙ ጥንዶች ሲለያዩ ማየቴ በጣም ያሳዝነኛል" ትላለች።

በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ጥንዶች ፍላጎታቸው ፍቅራቸው

ዘለቄታዊነት እንዲኖረው ከሆነ የሚያስፈልጓቸው መሰረታዊ ነገሮች አሉ።

ሳራ ለግንኙነት ረጅም ዕድሜ ወሳኝ የሆኑ ነገሮችን ለይታ ትናገራለች። ከነዚህ ነገሮች አንዱ ጥንዶች በችግሮቻቸው ላይ ለመስራት ጠንካራ ሆነው መቆየታቸው ነው። ሌላው በኢኮኖሚ ጠንካራ እንዲሆኑ ማድረግ እና በሌሎች ላይ ጥገኛ መሆን ሳይጠበቅባቸው በነጻነት ህይወታቸውን እንዲመሩ ማስቻል ነው። ስርዓተ ፆታዊ መድልዎ እንዲሁ ሚና ይጫወታል በመሆኑም ሴቶች እራሳቸውን ለማብቃት ጠንክረው መሥራት አለባቸው ትላለች።

በማህበረሰብ ደረጃ ማህደር እርስበርስ ለመተጋገዝ የተሻለ መንገድ መፈለግ እንዳለብን አጥብቃ ትናገራለች። በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሰዎች ለመደጋገፍ ገንዘብ ቢያሰባስቡም፣ በጋራ ጊዜ የሚያሳልፉት ለማህበራዊ ግንኙነት ብቻ እንጂ አውርተው ችግር ለመፍታት አይደለም። እነዚህ ዝግጅቶች እና ስብሰባዎች የአብሮነት ስሜት ለመፍጠር አስፈላጊ ናቸው። በተጨማሪም ግን ለተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ማህበረሰቡ ጠቃሚ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።

“ፓርቲዎች አሉ። ለመጠጣት እና ለመደነስ ተሰብስበሽ ሁሉም በራሱ ጊዜ ካሳለፈ በኋላ ሁሉም በየራሱ መንገድ ይሄዳል፡፡” ስትል ማህደር ትናገራለች፡፡ “ባለፈው ሳራ ወደአንድ ዝግጅት ወስዳኝ ነበር። ሁሉም ከሚያውቀው ሰው ጋር አንድ ላይ ሆኖ በላን ጠጣን የሚደንሰው ደነሰ ከዚያም ተለያየን። እንደዛ ከሚሆን ጠቃሚ ስለሆኑ ነገሮች ብንወያይ ጥሩ ነው።”

ሳራ በማህበረሰቡ ውስጥ ግልጽ ውይይት መኖር እንዳለበት እና እርስበርስ ለመረዳዳት ጠንካራ ትስስር መገንባት እንዳለበት ትስማማለች።

“ውይይት ብዙ ነገር ይቀይራል። መተሳሰብ እርስ በእርስ አንዳችን ለአንዳችን አለሁ መባባል እንዲኖር ያደርጋል። የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ማሪያም መድሃኒያለም እየተባለ ሰው ማህበር በመመስረት በደስታም በችግር ጊዜ ሲተጋገዝ ታያለሽ። እኛ ጋር እንደዚህ የምናደርግበት አጋጣሚ የለንም። እውነት ለመናገር ብዙዎቻችን የመጠጥ ብቻ ጓደኞች ነን ። እና ይህ ነገር ቢቀየር በጣም የተሻለ ማህበረሰብ ይኖረናል፡፡ ስለማንነቴ ግልጽ ከሆንኩ ከአስር አመት በላይ ሆኖኛል። በነዚህ አመታት የጠፉ ብዙ ጓደኞች አሉኝ። አማራጭ ስለሌላቸው፤ ወይ ያገባሉ ወይ ተስፋ በህይወታቸው ራሱ ተስፋ ይቆርጣሉ። እና ይሄ ነገር ቢስተካከል ብንተሳሰብ ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ።”




“

**የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ማሪያም መድሃኒያለም እየተባለ ሰው ማህበር በመመስረት በደስታም በችግር ጊዜ ሲተጋገዝ ታያለሽ። እኛ ጋር እንደዚህ የምናደርግበት አጋጣሚ የለንም።**

ሳራ

# የፍቅር ግንኙነት .የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነት

በ20ዎቹ መጀመሪያ ላይ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነቱን እንደተቀበለ ሰው የፍቅር ግንኙነትን ውስብስብ ሆኖ አገኘዋለሁ። ከሃይማኖታዊ አስተምህሮዎችን አለመላቀቄ እና ራሴን መገደቤ አዲስ ሰውን ለማወቅ እንዳልሞክር የመረጥኩት ምርጫ ላይ የራሱ ሚና አለው። ነገር ግን  ለራሴ እውነተኛ ልሁን ካልኩ ከመለያየት ጭንቀት ራሴን ለመጠበቅ ስል ሰዎችን ማራቄ፣ በዛ ላይ የተመሳሳይ ጾታ የፍቅር ግንኙነት ውስጥ ያሉ የሚጠበቁብኝ መስፈርቶች ትልቁን ሚና ይጫወታል።

ለየብቻም አብረንም ማደግ እንድንችል እድልን የሚፈጥር ፍቅርና መከባበር ያለው ግንኙነት ፈልጋለሁ። የፍቅር ጉዞአችን ላይ ጥልቅ ቅርርብን እመኛለሁ። ግን ደግሞ መተውን ወይም መጎዳት ያስፈራኛል። ብዙ ነገር እያጣሁ፣ እያመለጠኝ እንደሆንም እረዳለሁ። በዚህ ልምዴ ውስጥ የተመሳሳይ ጾታ ፍቅርን የሚገልጽ ምንም የተለየ ነገር የለውም ምናልባት አብዛኞቹ ጥቁር ወይም አፍሪካዊ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ከቤተሰባቸው ከደረሰባቸው የመተው ፍራቻ በመነሳት በሰዎች ላይ ያላቸው እምነት ላይ ተጽእኖ መፍጠሩ ሊያመሳስለው ይችላል። አስቀድሞ በሚፈጠር የመተው ጭንቀት ራስን የማራቅ ዘይቤ ከዛ ተቃራኒ የሆኑ አስተማማኝ የአብሮነት ዘይቤ ካላቸው ሰዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነትን በመፍጠር ሊሻሻል ይችላል የሚል ነገር አንብቤ ነበር። ለዚያም ፣ ወደፍቅር ዓለም ስለመግባት ብዙ ጊዜ አስባለሁ። አልፎ አልፎም ለዚህ ተብለው የተዘጋጁ የሞባይል መተግበሪያዎችን እጠቀማለሁ።

> “
>
> **ለየብቻም አብረንም ማደግ እንድንችል እድልን የሚፈጥር ፍቅርና መከባበር ያለው ግንኙነት ፈልጋለሁ። የፍቅር ጉዞአችን ላይ ጥልቅ ቅርርብን እመኛለሁ።**

በተመሳሳይ ጾታ የፍቅር ግንኙነት ዙሪያ ያሉ ጫናዎች እና የወሲብ ህይወቱ ምን ሊመስል እንደሚችል ማሰቡም ወስኜ እንዳልገባበት ይይዘኛል። የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ላይ ፍላጎት የለኝም የሚለውን እርግጠኛ አይደለሁም ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ አግባብ ያለው ከፍቅር ግንኙነት ውጪ የሆነ ወሲብ አለመፈጸሜ እንግዳ ነገር ሆኖ ይሰማኛል። ታሪክ በሚነግረን ብዙ ምክንያቶች የተነሳ ስለ ተመሳሳይ ጾታ ወሲብ በግልፅ የመናገር አስፈላጊነቱን እረዳለሁ፣ ሙሉ በሙሉ እደግፈዋለሁ።

ነገር ግን ይህን ግንኙነት እንዲከበር ወይም ልክ አይደለም ተብሎ የሚታሰበውን አመለካከት መቀየር ላይ ያለው አትኩሮት ከሌላ ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ጋር ወሲብ እስካላደረኩ ድረስ የማህበረሰቡ አካል እንዳልሆንኩ እንዲሰማኝ አድርጎኛል።

ሁሉም የዚህ ማህበረሰብ አባላት በተለይም ወንዳወንድነት የሚታይብንን *በቂ* የሆነ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ልምድ እንዲኖረን የሚጠብቅ በሚመስል የፍቅር ግንኙነት ዓለም ውስጥ እንዴት ልግባ? ማራኪ ሆኖ ካገኘሁት ከማንኛውም ሰው ጋር የጾታዊ ማንነቴን የሚገልጽ ወሲባዊ ሚናን ለመያዝ መጠበቁ እንድጨነቅ ያደርገኛል። በተመሳሳይ ጾታ የውበት መስፈርት መለኪያ እንደ “ማራኪ” ከሚታዩ ሰዎች ጋር ተገናኝቼ ምንም ፍላጎት ሳይሰማኝ ቀርቶ ያውቃል። ምናልባት ችግር አለብኝ ብዬ እንዳስብ አድርጎኛል፡  እንደነዚህ ያሉት ገጠመኞች የፍቅርም ሆነ ወሲባዊ ግንኙነት ለመገንባት እና ሙሉ በሙሉ ለመሳተፍ  አስቸጋሪ እንዲሆንብኝ አድርጎኛል።

የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ መሆኔን ከማመሰግንባቸው ምክንያቶች አንዱ ህይወቴን ነጻነት ያለው መስሎ እንዲሰማኝ ስላደረገ ነው፡፡ በርግጥ ይህ አለም ከተለያዩ ውስን መለያዎች እና ስለወሲብ ሲወራ ከሚነሱ የተሳሳቱ አመለካከቶች ነጻ አይደለም። እኔ እንደማስበው የፍቅር ጓደኝነትን በተመለከተ ተጨማሪ ውይይት ማድረግ የምንችል ይመስለኛል በተለይም የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን አስመልክቶ በአብዛኛው የተመሳሳይ አፍቃሪ ዘንድ ያለው መረዳት ሁሉንም ሰው እንደማይወክል ማወቅ ተገቢ ይመስለኛል።



# ማስታወሻ

ለመጀመሪያ

# ፍቅሬ



# የመጀመሪያ ፍቅር - መኖሪያዬ ነበረች፤ የህይወቴ አመላካች

> “ረድታኛለች ከሩቅ እንኳን ሆና ክንፌን የሚሰብር ከፍታ ቢሆን እንኳን ሳልፈራ እንድበር ታበረታኛለች። አሁንም ወደዚህ አዲስ ነገር ለመብረር መርጫለሁ።

በጆአን አርማትራዲንግ ፍቅር እና መውደድ ሙዚቃ ውስጥ አለች። በ2 ደቂቃ ከ50 ሰከንድ አካባቢ የሚሰማው ሳክስፎን የዘፈኑ በጣም የምወደው ክፍል በመሆኑ እንዴት እንደሳቀች ያስታውሰኛል። ከአርማትራዲንግ ጋር ያስተዋወቀችኝ እሷ በመሆኗ ሙዚቃውን ስሰማ ጨለማዎቹን የክረምት ቀናት፣ ብሩህ ፈገግታዋን እና አንዳንዴም ጮክ ብላ የምትስቀውን ውብ ሳቋን ያስታውሰኛል።

በግሎሪያ አንዛልዱዋ፣ በኦድሪ ሎርድ፣ በፓት ፓርከር እና በሌሎችም ብዙ አሳቢዎች እና ድንቅ ጸሃፊዎች የተጻፈ ጽሁፍ ባነነብኩ ቁጥር አገኛታለሁ። በየምሽቱ አልጋችን ውስጥ ሆነን አብረን እናነብ ነበር። ሁሌም እሷን የሚገልጻትን ዓረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ ጮክ ብላ ታነብ ነበር። እነዚህ ጸሀፊያን ያወኳቸው እሷን ከማግኘቴ በፊት ቢሆንም ለእነርሱ ያላት አክብሮት ዛሬም ድረስ ስማቸውን ስሰማ እሷን ብቻ እንዳስብ አድርጎኛል። አንድ ጊዜ ደረቷ ላይ ተኝቼ ሙሉ መጽሀፍ አነበበችልኝ፤ በመጽሀፉ ልቤ የተወሰደውን ያህል ድምጿና ከስር የሚሰማኝ የልብ ምቷ ሀሳቤን ሰርቆት ነበር።

መናፈሻው ውስጥ ስራመድ አገኛታለሁ። በማገኘው እያንዳንዱ የሂቢስከስ (ከርከዴ) እና ቦገንቪሊያ ተክል ውስጥ አያታለሁ፡፡ ዓይኖቿ ተክሎቹን ስላዩ ብቻ ያበሩ እንደነበር አስታውሳለሁ። ወይንጠጅ ቦገንቪሊያን ከሁሉም አስበልጣ ትወዳለች። እነዚህን እፅዋት ያሉበትን ቦታዎች እየፈለኩ እሷን እዛ መውሰድ ውስጤን በደስታ ይሞላው ነበር። ይህን የማደርገው ከሷ ጋር መሆኑ ደግሞ ደስታዬን እጥፍ ያደርገዋል፤ ደማቅ አድናቆት እና ደስታዋ አለምን ሁሉ ብሩህ ለማድረግ የሚበቃ ሀይል አለው፡፡

ህይወት ውስጥ አገኛታለሁ። ለምንም የማትበገር ነበረች...ልቧ ውስጥ ቤት ብገነባ መሰረቱ እድሜ ልክ እንደሚኖር የምተማመንባት.. ሳንገራግር የተረጋጉ እጆቿን ለመስጠት ሁሌም ከጎኔ ነበረች፡፡ በፅናት እና በጥንካሬ እንደምመለስ ታስታውሰኛለች። በዙሪያዬ ባለው ኢፍትሃዊነት ስሰላች እና ስበሳጭ ንዴቴን እንደ አብዮታዊ ጽናት ተረድታ ታበረታኛለች።

በየአንዳንዱ ቀን ውስጥ አገኛታለሁ። ከሩቅ ሙቀት ትሰጣለች... ክፍሉን አሻግራ በምታየኝ አስተያየት ብቻ ትገራኛለች። ምንም ሳትናገር ብዙ ትላለች። እንደቀልድ ስትነካኝ የሚሰማኝ ስሜት፣ እጅከፍንጅ የምይዛቸው እይታዎቿ፣ በገላዬ ላይ በለሆሳስ የሚሄዱ ጣቶቿ መከፋቴን/የአለምን ክፋት ሁሉ ያስረሱኛል። የማትገመት ሁሌ አዲስ ነበረች። ለመስጠትም ለመቀበልም ዝግጁ. ሁለቱንም በትልቅ ግርማ የምትተገብር።

ሕይወት በምትፈትነኝ ፈተናዎች ውስጥ ሁሉ አገኛታለሁ። በቀላሉ አትተወኝም። ሁሌም ጥሩ እንድሆን አጥብቃ ትነግረኛለች - ለሰው አሳቢ፣ እውነተኛ ፣ ሰው አክባሪ፣ አዳማጭ እና ደግ እንድሆን ትነግረኛለች፤ እሷም እነዚህ ሁሉ ሆና ታሳየኛለች። ሳላደርገው ስቀር ቃላት አታሰማምርም። እውነቱን ትነግረኛለች፡፡ መስመሬን እንዳለቅ እና ለማደርጋቸውም ለማላደርጋቸውም ነገሮች ሀላፊነት እንድወስድ ታስገድደኛለች። ግን ጭቅጭቃችን ወደ ጥል ሳይሆን ሁሌም አንዳችንን ወደአንዳችን ይመራናል። ልዩነቶቻችንን ደብቀን ከማባባስ ይልቅ አውጥተን እናወራበታለን። ይበልጥ ያቀራርበናል ምክንያቱም በምክንያት መከራከርን ተምረናል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን አንዳችን ለሌላው ያለንን ፍቅር ወይም ቁርጠኝነት አንጠራጠርም።

አሁን ላይ በምንለዋወጥባቸው ኢሜይሎች ውስጥ አገኛታለሁ። ከነዚህ

ሁሉ አመታት በኋላም እናወራለን - በመሀላቸው ያለው ከፍቅርም የሚበልጥ ሀይል መሆኑን የተረዱ ሁለት የተዛመዱ ነፍሶች፡፡ እሷ አሁን ደስ የሚሉ ልጆች ያሏት ባለትዳር ሴት ነች። ልጆቿ ልብ የሚነካ ፈገግታዋን፣ ግልጽ እና ተግባቢ ስብዕናዋን ከሗ ወስደዋል። ስለ ልጆቿ ከምሰማቸው ታሪኮች ሁሉ፣ ሚስቷ እና እሷ ደስተኛ፣ ጠንካራ እና ጽናት ያላቸውን ልጆችን እንዳሳደጉ እረዳለሁ፡፡

ያለፈውን ህይወቴን ወደሗላ መለስ ብዬ ሳይ አገኛታለሁ። ርቀት አለያየን። ምናልባት፣ አሁን የማውቀውን ባውቅ ኖሮ፣ የዚህ አይነት ፍቅርን ማግኘት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ባውቅ ኖሮ መቼም ላለቃት እይዛት ነበር።

በቅርቡ ለራሴ ማለም የጀመርኩትን ወደፊት ሳስብ በውስጡ አገኛታለሁ። ቤቴ ነበረች፣ የህይወቴ አመላካች እውነተኛ የህይወቴን አቅጣጫ ማወቅ ባልቻልኩ ጊዜ ሁሉ እንኳ የነፍሴ ጥሪ ነበረች። አፍቃሪን እና የፍቅር ግንኙነት የምለካበት መለኪያዬ ሆናለች። አስቤ የወሰንኩት ውሳኔ አልነበረም። ውስጤ እሗን፣ ከሗ ጋር የነበረኝን ስሜት ልክ እንደ መሰረታዊ መስፈርት መፈለግ ማቆም አልቻለም። የመሰማት፣ የመታየት እና የመረዳት ስሜት..

በሌላ አዲስ ጅማሬ የማውቀው የሚመስል ግን ደግሞ ከሗ ጋር ከነበረኝ የተለየ የሚመስል አዲስ ህይወት ጫፍ ላይ ቆሜ ራሴን ድጋሚ ወደሗ የቀረብኩ መስሎ ሲሰማኝ አገኘዋለሁ። ረድታኛለች ከሩቅ እንኳን ሆና ክንፌን የሚሰብር ከፍታ ቢሆን እንኳን ሳልፈራ እንድበር ታበረታኛለች። አሁንም ወደዚህ አዲስ ነገር ለመብረር መርጫለሁ። የአርማትራዲንግ ቃላትን ተውሼ አሁን ልክ እንደ መጀመሪያው ጊዜ፣ በቁርጠኝነት፣ በፍቅር እና በእውነተኛ ስሜት ልገባበት መርጫለሁ።

የመጀመሪያ ፍቅሬ ነበረች። እንደቤቴ ሰላም ከሚሰጠኝ ነገር ያነሰ ምንም እንዳልቀበል ያሳመነችኝ ፍቅሬ ነበረች።





# የከፍታ ውጊያ

## መስህብን መረዳት

ራሴን ግልፅ
አድርጌም
ስላልወጣሁ ሁለት
አለምን መኖር
ዩከብደኛል።
ኦንላይን ዴቲንግ
ሞክሬ ነበር ግን
በቃ ያቅተኛል፤
ለራሴ ምክንያት
በመስጠት
እርቃለሁ።

ከወንድ ጋር የፍቅር ግንኙነት ለመጀመሪያ ጊዜ የኖረኝ ሰባተኛ ክፍል እያለሁ ነው። የልጅነት ነገር ሆኖ ከእሱ ጋር ተለያይቼ ዘጠነኛ ክፍል ስገባ ነው የመጀመሪያ ፍቅር ብዬ ያሰብኩትን ግንኙነት የጀመርኩት። ስሙ ሱራፌል ነበር። ከሱራፌል ጋር በጣም እንግባባ ነበር፡ ስሜቴን በደንብ ያዳመጥኩበት እና ሙሉ ጊዜዬን የሰጠሁበት የፍቅር ግንኙነት ነው።

በጊዜው አብዛኞቹ የት/ቤት ጓደኞቼ ከፍቅር አጋሮቻቸው ጋር የወሲብ ግንኙነት ነበራቸው። እኔ ግን በፍፁም የምቃወመው ነገር ነበር። በእርግጥ ሃይማኖተኛ አልነበርኩም ግን ለምን እንደሆነ አላውቅም ለወሲብ ፈፅሞ ፈቃደኛ አልነበርኩም። ከፍቅረኛዬ ጋር በደንብ እንግባባ እና እንዋደድ ነበር። ከዘጠነኛ ክፍል እስከ አንደኛ አመት የዩኒቨርስቲ ትምህርቴ ድረስ አብረን ቆይተን ግን ተለያየን። ዩኒቨርስቲ ስገባ በጣም ሃይማኖተኛ ሆንኩ፣ አክራሪ ሃይማኖተኛ በሚባል ቤተሰብ ውስጥ አይደለም ያደኩት ነገር ግን የእኔ አመለካከት ተቀየረ። ዘወትር ሂጃብ ማድረግ ጀመርኩ፣ ከወንድ ጋር አልጨባበጥም፣ ከሱራፌል ጋር የተለያየነውም በዚህ ምክንያት ነው።

ከሱራፌል ጋር ከተለያየሁ በኋላ ነበር የመጀመሪያ አመት ትምህርቴን ልጨርስ አካባቢ ከባለቤቴ ጋር የተገናኘነው። ሰሚር የእስልምና እምነት ተከታይ፣ የተማረ እና ጠንካራ ሰራተኛ ነው። እኔ አስራ ስምንት ወይም አስራ ዘጠኝ አመቴ ነበር። እንደአንድ የእስልምና እምነት ተከታይ ሃይማኖተኛ በፍቅር ግንኙነት ውስጥ ምንም ማድረግ አይፈቀድም። መሳሳም፣ ወሲብ መፈጸም... ሁሉም ክልክል ነው። በዛ እድሜ ላይ ቀለል አድርጌ ስላሰብኩት እና ከሰሚር ጋር አብሬ የፈለኩትን ለማድረግ ስል ይመስለኛል ከሁለት አመት በኋላ ኒካ አሰርኩኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወሲብ አደረግን ግን በጭራሽ አልወደድኩትም። መሳሳሙ ደስ ይለኛል ግን በድጋሚ

“

**ከሰሚር ጋር አብሬ የፈለኩትን ለማድረግ ስል ይመስለኛል ከሁለት አመት በኋላ ኒካ አሰርኩኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወሲብ አደረግን ግን በጭራሽ አልወደድኩትም። መሳሳሙ ደስ ይለኛል ግን በድጋሚ ለማድረግ ምንም ፍላጎት አልነበረኝም።**

ለማድረግ ምንም ፍላጎት አልነበረኝም። ምክንያቱ ምን እንደሆነ ማወቅ አልቻልኩም ግን በቃ ፈፅሞ ደስተኛ አልነበርኩም።ምክንያት እየፈጠርኩ አላገኘውም ነበር። ትምህርቴን ስጨርስ ያው የሚጠበቀው እንድንጋባ አብረን እንድንኖር ነው እኔ ግን ምንም አይነት እንደዛ አይነት እቅድ አልነበረኝም።

የሁለተኛ አመት ተማሪ እያለሁ ግቢ ውስጥ አንድ ልጅ አየሁ ፤ በህይወቴ እንደዛ አይነት ቆንጆ ሴት አይቼ አላውቅም... መብረቅ የመታኝ ነው የመሰለኝ። አስታውሳለሁ ወደዶርሜ እየሮጥኩ ተመለስኩ እና ለጓደኞቼ ነገርኳቸው። ዶርም ውስጥ ተሳቀብኝ... ከሁለት ወይም ሶስት ወር በኋላ በድጋሚ ከሩቅ አየኋት። ለጓደኞቼ በደስታ ነበር የነገርኳቸው ግን ለምን መተዋወቅ እንደፈራሁ ለሁላችንም ግልፅ አልነበረም።

ከብዙ ጊዜ በኋላ ነበር ደረጃ ላይ በአጋጣሚ ተገናኘን። በድንጋጤ ሀይ አልኳት። እሷም ፈገግ ብላ ሀይ አለችኝ። ድንጋጤዬን ያወቀችብኝ ይመስለኛል ብቻ እየሮጥኩ አልፌያት ሄድኩ። ተሰምቶኝ የማያውቅ አይነት ጥልቅ ስሜት ነበር። ምን ማድረግ እንደነበረብኝ ስላላወኩ ደግሜ አላናገርኳትም፡፡ ለኔ አዲስ ስሜት ነበር። ከጾታዊ ዝንባሌ ምርጫዬ ጋር ለማያያዝ በወቅቱ በቂ እውቀት አልነበረኝም፣ በውበቷ ተስቤ ነው ብዬ ለማለትም ከባድ ነበር። ያ በዚህ አለፈ።

ሌላኛው ከፈሪድ ጋር የነበረኝ ትውውቅ ነው፣ ግቢ የተዋወኳት ሌላ ውብ ሴት። የጓደኞቼ ጓደኛ ነበረች እና በነሱ በኩል ቀስ በቀስ ተግባባን። ይበልጥ የተግባባነው የሆነ የትምህርት ስልጠና ላይ እኔ እና እሷ ተመርጠን ወደሌላ ክልል የሄድን ጊዜ ነው። በጣም ብዙ ወንዶች ይፈልጓት ነበር እና እኔ በጣም እጠነቀቅላት ነበር። እሷ ለአንዳቸውም ምንም ፍላጎት አታሳይም እና እኔ ጣልቃ ገብቼ አትፈልግም እላቸዋለሁ። ያ ስልጠና በጣም አቀራረበን፥ አብረን ብዙ ጊዜያችንን እናሳልፍ ጀመር። የሚገርመው ወንዶች ሲያስቸግሯት ቦይፍሬንድ አለኝ ብላ እኔን ነበር የምትነግራቸው። ነገር ግን ስለየትኛውም ነገር ግንዛቤው አልነበረኝም። አስታውሳለሁ ሰሚር በግንኙነታችን ደስተኛ አልነበረም። አብዛኛውን ጊዜዬን ከሷ ጋር ነው የማሳልፈው ፤ በዛ ምክንያት ደስተኛ አልነበረም። ከፈሪድ ጋር ከሰኞ እስከ አርብ ካምፓስ ውስጥ አንለያይም፣ ቅዳሜ እና እሁድም ሲመጣም ግን አብረን ነበር የምናሳልፈው።

ተመርቀን ከወጣን በኋላ እኔና ፈሪድ መስሪያ ቤታችን ቅርብ ለቅርብ ነበር እና ከስራ በኋላ አብረን እናመሻለን። በዚህ ሁኔታ ከሰሚር ጋር ለስድስት አመት ቆየን። ከዛ በኋላ ወደ አሜሪካ የመምጣት እድሉ ገጠመኝ፤ እውነት ለመናገር ከሱ ጋር መለያየቴ በጣም ነበር ደስ ያለኝ። በርቀት ለመቀጠል ሞከርን፥ ስልክ ይደውል ነበር

ግን ለኔ በጣም የሚያስጨንቅ ጊዜ ነበር። ለምን እንደሆነ በወቅቱ ባላውቅም ከሱ ጋር ያለኝን ነገር ማቆም ፈልጌ ነበር። አሜሪካ ከሄድኩ በኋላ ለአንድ አመት ከሱ ጋር ከቆየን በኋላ ምን እንደተፈጠረ አላስታውስም ግን ግንኙነቱን አልፈልግም አልኩ።

አሜሪካ ከመጣሁበት ቀን ጀምሮ በየቀኑ ከፈሪድ ጋር እናወራ ነበር፥ ከሶስት አመት ቆይታዬ በኋላ ፈሪድም ከነቤተሰቧ ወደ አሜሪካ መጣች። የተለያየ ከተማ ብንሆንም ጓደኝነታችን ግን በዛው ቀጠለ። ዛሬም ድረስ ከሷ ጋር ያለኝ ግንኙነት ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም ግን በጣም ልዩ የሆነ ግንኙነት ነው ያለን፡፡ አሜሪካ ስትመጣም በጣም ነበር ደስ ያለኝ። ስለጾታዊ ዝንባሌ ምንም አይነት እውቀቱ አልነበረኝም፤ የተለያየ አይነት ፍላጎት መኖሩንም አላውቅም ነበር። የልጅነት ፍቅረኛዬ የሆነ ወቅት ወደአሜሪካ መጣ እና ከሱ ጋር ወሲብ ለማድረግ አስበን ነበር፡፡ ስንገናኝ ግን ምንም ፍላጎት ሊኖረኝ አልቻለም፤ ማመን አቃተው። የሚገርመው በምን አስቦት እንደሆነ አላውቅም የወንድነት ጉራ አለ አይደል እንዴት ለኔ ፍላጎት አይኖራትም ይሁን ብቻ አላውቅም ግን 'ሴት ነው የምትወጂው?' ብሎ ጠየቀኝ፡፡ በጣም ነው የደነገጥኩት እና እንዴት እንዲህ ትለኛለህ ስለው ወሬውን ወዴት ማስኬድ እንዳለበት ስላላወቀ "አይ ዝም ብዬ ነው የጠየኩሽ" አለኝ። ምን አስቦ እንደሆነ አላውቅም ፤ አሁን ጥሩ ግንኙነት አለን እና መጠየቅ አለብኝ።

ከዛ በኋላ ይሄ ነገር ምንድን ነው ብዬ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ይመስለኛል ከተለያዩ ወንዶች ጋር ግንኙነት የኖረኝም አብሬ ለመተኛት የፈለኩትም ውስጤ የነበረውን ነገር ላለማዳመጥ ነበር። ጥሩ ግንኙነት ካለኝም ወንድም ጋር ምንም የወሲብ ስሜት የማድረግ ፍላጎት ከሌለኝ ምንድን ነው ችግሬ ብዬ ማሰብ ጀመርኩ። ሌላም ተመሳሳይ አጋጣሚ እንዲሁ ተፈጥሮ ነበር፥ አንድ ልጅ ተዋውቄ ወሲብ ለማድረግ ግን ምንም ፍላጎት አይኖረኝም እና እሱ ራሱ ግራ ገብቶት "ሴት ነው እንዴ የምትወጂው?" አለኝ። ማመን አቃተኝ፤ በጣም ደነገጥኩ። አሁንም ሸፋፍኜው አለፍኩ።

ያንን ማንነቴን ለመካድ ብዙ ነው የሞከርኩት። ከአመታት በኋላ ነው እንደገና ስለማንነቴ ማሰብ የጀመርኩት፥ ምናልባት ፍላጎት ያለኝ ለሴት ነው ወይም ወሲብ በአጠቃላይ አልወድም ማለት ነው ብዬ ማሰላሰል ጀመርኩ። በዛ ሰሞን ወደ አንድ ከተማ ከፈሪድ ጋር ለሰርግ እንሄድ ነበርና ያ ከተማ በጣም የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች የሚታይበት ከተማ ነበር እና ሳላውቀው ሰዎች እንዳያውቁብኝ ፈለኩ፤ በርግጥ ምንም የማውቀው ነገር ኖሮ አይደለም፡፡ ለመደበቅ የፈለኩት ራሱ ምን እንደሆነ ግልፅ አልነበረልኝም። የሚገርመው ከዛ ወዲህ ለፈሪድ በጣም መጠንቀቅ ጀመርኩ፤ ሳስባት ራሱ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማኝ ነበር፥ ያለንን የቅርብ ጓደኝነት ማጣት አልፈልግም።

ከዛ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ ነው እንግዲ ራሴን የተቀበልኩት። አሁን ራሴን አውቄና ተቀብዬ መኖር ከጀመርኩ ወደ 10 አመት ይሆነኛል። ነገር ግን ከሴት ጋር የፍቅር ግንኙነትም ይሁን ወሲብ አድርጌ አላውቅም። ለዚህም አብዛኛው ምክንያት ማህበረሰቡ እና ሃይማኖቴ ነው። ራሴን ብቀበልም ሃይማኖቴ ራሴን እንድሆን ቦታ ስላልሰጠኝ ብዙ ነገሬን ከዛ አርቄ እንኚን ከሴት ጋር ግንኙነት መፍጠር ይከብደኛል፡፡ ራሴን ግልፅ አድርጌም ስላልወጣሁ ሁለት አለምን መኖር ይከብደኛል። ኦንላይን ዴቲንግ ሞክሬ ነበር ግን በቃ ያቅተኛል፤ ለራሴ ምክንያት በመስጠት እርቃለሁ። በዚህ ሁሉ አመታት ውስጥ የፍቅር ግንኙነት ቢቀር እንኳን የወሲብ ግንኙነት ያልነበረኝ የማደርገውን አውቃለሁ የሚለውን ጥያቄ መመለስ አለመቻሌ እና በቂ አይደለሁም የሚለው ፍራቻ ይዞኝ ነው። ቤተሰቤን እና አካባቢዬን አስብና ውጥረት ውስጥ እገባለሁ። ብቻዬን ነው የምኖረው እንዲሁም የራሴ ገቢ ነው ያለኝ ነገር ግን ከቤተሰቤ ጋር ያለኝ የቅርብ ግንኙነት ራሴን ገፍቼ እንዳላውቅ አድርጎኛል።

> “
>
> **አሁን ራሴን አውቄና ተቀብዬ መኖር ከጀመርኩ ወደ አስር አመት ይሆነኛል። ነገር ግን ከሴት ጋር የፍቅር ግንኙነትም ይሁን ወሲብ አድርጌ አላውቅም። ለዚህም አብዛኛው ምክንያት ማህበረሰቡ እና ሃይማኖቴ ነው።**

*

# ነኝ

የራሳችንን ታሪኮች በራሳችን ለመናገር እምብዛም እድሉን አናገኝም ፤ እድሉን ባገኘንባቸው ጥቂት ጊዜያትም የምንነግራቸው ታሪኮች ከመከራ ወይም ከጭንቀት የመነጩ ናቸው። በጥላቻ በተሞላ አካባቢ ውስጥ ሆኖ የኲዊር ሕይወትን መምራት ቀላል ባይሆንም በየቀኑ እራሳችንን በመሆናችን ብቻ ዓለማችንን እንሞግተዋለን እናም እንቀይራለን ብለን እናስባለን። ነገር ግን ስቃያችን ብቸኛዉ መለያችን አይደለም። ከራሳችን የወጡ እና ያልተበረዙ፣ እውነተኛ የደስታ ጊዜዎች አሉን።

ነኝ እነዚህን ታሪኮች ለመንገር ከመነጨ ፍላጎት የተጠነሰሰ አዲስ መጽሄት ነው።

**በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ይከተሉን።**
**Facebook:** www.facebook.com/negne.ET
**Instagram:** www.instagram.com/n.e.g.n.e



## ከሴት ተመሳሳይ ጾታ ፍቅር ግንኙነት መውጣት

# ጓደኝነትን ማስቀጠል





ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሴት ነኝ:: ተቀባይነት በማይገኝበት ሃገር እና ማህበረሰብ እንደሚኖር እንደአብዛኛው ተመሳሳይ ፃታ አፍቃሪ ሴት ራሴን "ለማስተካከል" ከተለይዩ ወንዶች ጋር የፍቅር ግንኙነትን መስርቻለሁ። እያደኩ ስመጣ የነበሩኝ የወንድ ጓደኞች ማንነቴን ይቀይሩታል ብዬ ያሰብኩት ከአካባቢዬ ባለው ጫና እንደሆነ ቢገባኝም የእውነት እኔ ሴት አፍቅሬ ኑሮን መኖርን ማሰብ ደግሞ ከባህልም ከሃይማኖትም ይጋጭብኝ ነበር።

በሃያዎቹ አጋማሽ ላይ ይበልጥ ወደቤተክርስቲያን በመቅረብ ለሴት ያለኝን ስሜት የቀበርኩበት ወቅት ነበር። በወቅቱ ከነበረኝ የፍቅር አጋር ጋር ለትዳር የታለመ ግንኙነት ነበረኝ። በምችለው ሁሉ ስለሴት ላለማሰብ እንዲሁም ከራሴ ጋር ይህንን ጥያቄ ላላሰላስል ወስኜ መኖር ጀምሬ ነበር። ህይወት ያልሆናችሁትን ለመሆን ስትወስኑ ያላት ፈተና መብዛቱ!

በስራ ምክንያት ከሄርሜላ ጋር ተዋወቅን። የመጀመሪያው ቀን ላይ በጣም ተግባብተን አብረን ብዙ ጊዜ አሳለፍን። ከዛን ቀን ጀምሮ በየቀኑ ቴክስት እንደራረጋለን፥ ብዙ ነገሮች ላይ ያሉን አመለካከቶች አንድ ስለሆኑ የምናወራው አናጣም ነበር።

የቀበርኩት ነገር ራሱን እየፈነቃቀለ እንደሆነ የገባኝ፤ ከብሩክ ጋር ከማውራት ይልቅ ሄርሜላን ስመርጥ፣ እሱ ከሚደውልልኝ ይልቅ ከሷ ጋር ረዥም

> “
> **ያን ሁለት ዓለም ህይወት እንዴት እንዳሳለፍኩት አላውቅም። ከሄርሜላ ጋር ብን ያለ ፍቅር ቢይዘኝም አብሮ መኖር ወይም ነገን ማሰብ አልቻልኩም፤ ራስን ሙሉ በሙሉ አለመቀበል ትልቁ ምክንያት ነው።**

ሰዓት ሳወራ እንዲሁም ከብሩክ ጋር ያለኝን ቀጠሮ እየሰረዝኩ እሷን ማግኘት ስጀምር ነው። እስካገኛት መጓጓቴ ያስፈራኝ ጀመረ ነገር ግን አለማግኘትን መምረጥ አልቻልኩም።

በሷ በኩል ያለውን ነገር ለማወቅ ጊዜ ወሰዷል። ከተዋወቅን ከወራት በኋላ ቤታቸው ሄጄ እንዲሁ እያወራን በቅፅበት ከንፈሯን ሳምኳት፤ ምላሽ አልነበረም። ደነገጥኩ ነገርግን ማውራት አልቻልኩም። ስለተፈጠረው ነገር ምንም ሳንባባል ያን ቀን ተለያየን።

ከዛን ቀን ጀምሮ ይበልጥ ድፍረት ኖረን። እንደናፈቀችኝ፣ እያሰብኳት እንደሆነ ሜሴጅ መላክ ጀመርኩ… የሚገርመው ከሷም በኩል ተመሳሳይ ሜሴጅ ይደርሰኝ ነበር። በአካል በግልፅ ማውራት ባንችልም በሜሴጅ መዋደዳችንን አፀደቅነው። የጥፋተኝነት ስሜት ሁሌም ከበስተጀርባዬ ቢኖርም ነገሮችን ደግሞ ማቆም አልፈለኩም። ከብሩክ ጋር ያለኝን ነገር ለማቆም የሚያበቃ የራስ መቀበል አልነበረኝም፤ ከሄርሜላ ጋር ደግሞ ያለውን ነገር ለማቆም የነበረኝ ፍቅር አላስቻለኝም።

ከብሩክ ጋር የነበረኝ ነገር እውነት እንዳልሆነ እየተገለጠልኝ ቢሄድም የሚጠበቅብኝን ወግ መዓረግ ለመብቃት ግትር ብዬ ነበር። ሶስት ዓመት ከሱ ጋር መቆየቴን ሳስብ ይገርመኛል።

ሄርሜላን ሁለተኛው አመት ላይ ነበር የተዋወቅኳት። ጊዜው በሄደ ቁጥር የኔ እና የሄርሜላ ፍቅር እየጠነከረ ሄደ። በየቀኑ እንገናኛለን፣ እንደዋወላለን፣ አብረንም እናድራለን።

ብሩክ ቤተሰቦቼ ስለሚያውቁት አብዛኛውን ቅዳሜ እና እሁድ ከቤተሰቤ ጋር ሆነን እናሳልፋለን። ያን ሁለት ዓለም ህይወት እንዴት እንዳሳለፍኩት አላውቅም። ከሄርሜላ ጋር ብን ያለ ፍቅር ቢይዘኝም አብሮ መኖር ወይም ነገን ማሰብ አልቻልኩም፤ ራስን ሙሉ በሙሉ አለመቀበል ትልቁ ምክንያት ነው።

ከብሩክ ጋር ስለትዳር ወሬ ቢነሳም ከመደሰት ይልቅ ይህ የሁለት አለም ህይወቴ እንዴት እንደሚቀጥል ያስጨንቀኝ ነበር። ሄርሜላ ብሩክ ፍቅረኛዬ እንደሆነ ስለምታውቅ ነገሮችን ለመረዳት ትሞክር ነበር። ብሩክ ስለዚህ ህይወቴ ምንም ስለማያውቅ ድብብቆሹ ቀላል የሚባል አልነበረም። በእውነት ባምንም እንዴት እዚህ ላይ እውነትን መናገር ይቻላል? ከሄርሜላ ጋር ያለኝ ነገር ደስታን እንደሚያመጣ ሁሉ ትልቅ ጭንቅ ውስጥም ከቶኛል። ለኔ ብቻ ሳይሆን ለሄርሜላም ቀላል አልነበረም።

ለሁለት አመት ያህል ከሄርሜላ ጋር አብረን ቆየን። በሁለት አመት ውስጥ ውሳኔዎቻችን አልተለውጡም፤ ግንኙነታችንን ወዴትም መቀየት ወይም ማሳደግ አልቻልንም። በዚህ መሃል እኔ እና ብሩክ ተለያየን። የሚገርመው ከተለይየን በኋላ እኔ እና ሄርሜላ ያለን ግንኙነት ራስን በመቀበል የታሰረ ስላልነበረ ይበልጥ ጭንቀት ውስጥ ከተተኝ፤ ብሩክ እያለ ከነበረው ውዝግብ ይልቅ አሁን ባለን “ነፃነት” ተጨነቅኩ። ከራስ ጋር ትግሉ ይበልጥ በረታ።

በዚህ ጊዜ ነበር ያለንን ግንኙነት ማቆም እንዳለብን የነገርኳት፤ ለሁለታችንም ቀላል አልነበረም። ከሁሉም ነገር የቅርብ  ጓደኛ ሆነን መቀጠል እንድንችል ተመኙሁ። ሄርሜላን በጣም ነው የምወዳት ስለተፋቀርን ብቻ ሳይሆን ማንነቷን በጣም እወደዋለሁ ፣ በቀላሉ እንግባባለን፣ እንስቃለን ፤ መልካም እንተሳሰባለን።

ጊዜ ወሰዷል! የፍቅር እና የወሲብ ግንኙነት ከነበራችሁ ሰው ጋር የቅርብ ጓደኛ ለመሆን ጊዜ ይወስዳል። ወሲባዊ ስሜትን መግታት፣ ተረጋግቶ መወያየት ቀላል አይደለም። ሄርሜላ እና እኔ በአራት አመት ጉዞ ውስጥ ራሳችንን የተተቀበልን ሌዝቢያን ጓደኛሞች ሆንን። ከሌላ ሴት ጋር ያለንን ግንኙነት በግልፅ እናወራለን፣ እንመካከራለን።  ያሳለፍነውን ጊዜ እያነሳን በልጅነታችን እንስቃለን። ዛሬ ላይ ሄርሜላ በህይወቴ ማጣት የማልፈልጋት የአራት አመት የቅርብ ጓደኛዬ ናት።

## “ከራሴ ጋር ግንኙነት መፍጠር ችያለሁ፤ እኔ እና ራሴ ብዙ ደግሞ የምናስሳቸው ነገሮች አሉ።”

ግንኙነት ወይም ትውውቅ የሚባለውን ነገር ለማቆም የወሰንኩት ክረምት 2011 ላይ ነው። ሃሳቡ የመጣልኝ ክረምት ላይ ከነበረኝ የአጭር ጊዜ ግንኙነት በኋላ ከማንኛውም አይነት ቅርብ ግንኙነት እረፍት ለመውሰድ ፈልጌ ነው። እናም ያንኑ አደረኩኝ፥ ጊዜዬን ወደ ጓደኞቼ፣ ወደ ሥራዬ፣ ወደ ጤንነቴና በመስጠት የሚያስፈልገኝን ሁሉ እያደረግኩ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር። ከዚያም የኮሮና ወረርሽኝ መጣና እየተቋቋምኳቸው እንደሆነ ያሰብኳቸው እነዚህ ሁሉ መንገዶች ፈራረሱ። ለጥያቄዎቼ መልስ የምሰጠው እኔ ብቻ ሆኜ ቤቴ ቀረሁ። ለማወቅ ጊዜ ወስጄ የማላውቃቸውን ሁሉንም የራሴ ክፍሎች ለማግኘት እታገል ጀመር። ስለዚህ ከባድ ጥያቄዎችን መጠየቅ ጀመርኩ፤ ስለኩዊርነቴ ማንነት ማንም ሳያየኝ ተማርኩ። ከሌሎች ጋር በነበረኝ ግንኙነት ከራሴ በፊት ለሌሎች የቆምኩትን መንገድ ተውኩ። ለሌሎች ስል መሆንንና ማስመሰልን አቆምኩ። በመጀመሪያ ለራሴ እንዴት መቆም እንዳለብኝ ተማርኩ (እየተማርኩም ነው)።

ከስርዓተ ፆታዬ ጀመርኩ፥ ራሴን ሴታሴት* ማድረጉን አቁሜ ገደብ የሌለውን የስርዓተ ፆታ ማንነቴን ተቀበልኩ። ፀጉሬን ተቆርጬ የሚመቸኝ ነገር ላይ አተኮርኩ። ይሄን ማንነት እንዴት ይገፍ መውጣት እንደምፈልግ እና የመሳሰሉ ብዙ ጥያቄዎች ብቅ አሉ። ማህበረሰቤ ፍቅርን እንዴት እንዳይና እንድረዳ ያሳደሩብኝን ተጽዕኖ መለስ ብዬ ገመገምኩት። በነሱ ጠባብ የሆነው አስተሳሰብ ውስጥ ለመስማማት ስል ራሴን ያሳነስኩበት መንገድ እጅግ አስለቀሰኝ። ስለማንነቴ የነበሩኝን አስተሳሰቦች አስወገድኩ።

አሁን ላይ በጣም ሰፊ የሆነው የኩዊር ማንነቴ አብሮኝ ቀርቷል። ከራሴ ጋር ግንኙነት መፍጠር ችያለሁ፤ እኔ እና ራሴ ብዙ ደግሞ የምናስሳቸው ነገሮች አሉ።

## “የፍቅር ጓደኛዬን ስስማት ግን ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማላውቀው ደስታ ተሰማኝ።”


የመጀመሪያ የፍቅር ግንኙነቴ ውስጥ ብዙ ችግሮች ነበሩ። የሁለታችንም ቤተሰቦች የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ እንደሆንን ስለማያውቁ ስለግንኙነታችንም አያውቁም ነበር። ግንኙነቱ በራሱ መጥፎ ገጽታዎች ነበሩት፣ እንደማመጥም ነበር። ተገናኝተን የፍቅር ግንኙነት ውስጥ ስንገባ ሁለታችንም 19 አመታችን ነበር። እየተጣላን እየታረቅን ወደ አንድ አመት እና ጥቂት ወራት ያህል አብረን ቆይተናል፡፡ ግን ይህ ግንኙነት የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነቴን አረጋገጠልኝ።

ሁሌም ቢሆን በሴቶች እንደምሳብ እና ከዚህ በፊትም ፍቅር ይዞኝ እንደሚያውቅ አውቀው ነበር። ከሴት ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኔ ግን ይህን እውነታዬን አረጋግጦልኛል። ወንዶችን ስሜ አውቃለሁ ነገር ግን ደስ ብሎኝ አያውቅም። የፍቅር ጓደኛዬን ስስማት ግን ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማላውቀው ደስታ ተሰማኝ።

ይሄም በፍቅር ግንኙነት ውስጥ ፍቅር እና ደስታ ሊሰማኝ የሚችል ሰው እንደሆንኩና ስለማንነቴ ይሰማኝ የነበረው ስሜት ትክክል መሆኑን አረጋግጦልኛል፡፡

# ስለ

## አንድ ለአንድ ስላልተወሰነ ትዳር





# ... የሁለትዮሽ ፆታ አፍቃሪነትን መመርመርና ከወንድ ጋር ትዳር

እኔ በአሁኑ ጊዜ ወንድ ባለቤት ያለኝ የሁለትዮሽ ጾታ አፍቃሪ ሴት ነኝ። በጊዜው ለመጋባት ዝግጁ አልነበርንም ነገር ግን በቤተሰባችን ከፍተኛ ጫና ይደርስብን ነበር። የተጋባንበት ዋናው ምክንያት ልጃችን ናት ምክንያቱም ቤተሰቦቻችን በወቅቱ ራሳችንን ለመጠበቅ ትክክለኛው ውሳኔ ህጋዊ የሆነ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ማግኘት ብቻ እንደሆነ አምነው ነበር። ለነበረን ግንኙነት ሳይሆን ለልጃችን ደህንነት ስንል ያደረግነው ነገር ነው።

ከስሜት አንፃር፣ ራሳችንን እንደምናየው እንዲሁ አብረው እንዳሉ ጥንዶች እንጂ በተለምዶው ባለትዳሮች የሚለው ቃል በሚይዘው ትርጉም አይደለም።

በግንኙነታችን መጀመሪያ ላይ የእኔ የሴትም የወንድም ፆታ አፍቃሪ መሆኔ ትልቅ ነገር ነበር፣ ብዙ ረጅም ውይይቶችን አድርገንበታል። የሚያስፈልገኝን ሁሉንም ነገር ከሱ ብቻ ማግኘት የማልችል መሆኔን እንዲያውቅ እና እንዲቀበል ነግሬዋለሁ። ደስ ይላል፣ ምክንያቱም አዳዲስ ነገሮችን መመርመር፣ መሞከር እና በነሱም መዝናናት እንድችል የሚፈልግ ክፍል በውስጤ አለ። ግን ደግሞ የፍቅር ግንኙነት ውስጥ ነኝ እናም ያንን ማክበር እፈልጋለሁ። እድሜዬ እየጨመረ ሲሄድ የማወቅ ጉጉቴም እንደዛው ጨመረ። የሁለትዮሽ ጾታ አፍቃሪ ማንነቴ ከምን ጊዜውም በላይ ጠነከረ እና ይበልጥ የማወቅ፣ የመለማመድ እና የመሞከር ፍላጎት ኖረኝ። ከአንድ ወንድ ጋር ግንኙነት ውስጥ ሆኜ ይህን ማድረግ ደግሞ ፈታኝ እና ከባድ ነው።

ከባለቤቴ ጋር ስለ ሃሳቤ በግልፅ መነጋገር መቻሌ እና ስለ እኔ የሚያውቀው ነገር መሆኑ ቀላል ያደርገዋል። ራሴን ለማግኘት ክፍተት ስለሚሰጠኝ በጣም አመሰግነዋለሁ። ይህን ክፍሌን ዝም ብዬ ማጥፋት እንደማልችል ያውቃል። ነገር ግን ይህን የሚቀበለኝ ለትክክለኛው ምክንያት ነው ወይ የሚለውን እርግጠኛ አይደለሁም። እንደ ተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ወንድ ለእሱ የሚታየው ምናልባት የሁለት

> “
>
> **እኔ ደግሞ ወሲባዊ ማንነቴን እና ከሌሎች ጋር ያለኝን ግንኙነት በጥልቅ መመርመር የምፈልግበት ቦታ ላይ ነኝ።**

ሴቶች አንድ ላይ መሆን የሚፈጥርበት ጉጉት እና ደስታ ነው። ለምሳሌ በጣም ሴታሴት ከሆነች ሴት ጋር የመሆን ፍላጎት ካለኝ በንግግሩ ውስጥ እንዲካተት እና ሦስታችንም አብረን እንድንወያይ ይገፋኛል። ነገር ግን ትንሽ ወንዳወንድ የሆነች ሴት ከሆነች ከኛ ርቀቱን ይጠብቃል ወይም እርግጠኛ ነሽ ብሎ ይጠይቀኛል። ከሌላ “ወንዳወንድነት” ከሚታይባት ሴት ጋር ብተኛ ወንድነቱን የሚፈታተን አድርጎ የሚያስበው ይመስለኛል።

እና ስለ ግንኙነታችን ሁኔታ ግልጽ የሆነ ውይይት አለማድረጋችን ትዳራችን አንድ ለአንድ የተወሰነ አለመሆኑን አስመልክቶ የሚፈጠሩትን ፈተናዎች እንዳናወራበት አድርጎናል። ምንም እንኳን አንድ ለአንድ ያልተወሰነ ትዳር ውስጥ ስለመሆናችን በግልፅ ተስማምተን ባናውቅም በተግባር ግን አብረን እያለንም ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዝናናለን፤ እንገናኛለን። ብቻ ትዳራችን ለሌሎችም ክፍት የሆነ እና እንደየሁኔታው የምንይዘው ነው ማለት ይቻላል።

በአሁኑ ጊዜ ባለን ግንኙነት ላይ እና እሱ ስለኔ የሁለቱም ጾታ አፍቃሪነት እንዲሁም ሌሎች የፍቅር አጋሮችን አስመልክቶ ያለው አመለካከት ላይ ጾታ ትልቅ ሚና አለው። ሴትነቷ ገኖ የሚታይ ከሆነች ያንን ግንኙነት የማጠንከር ፍላጎቱም እንደዛው ከፍ ያለ ነው። ሁሌም የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ከሆኑ ሴቶች ጋር ብቻ ነው ግንኙነት ኖሮት የሚያውቀው። እኔ ደግሞ ወሲባዊ ማንነቴን እና ከሌሎች ጋር ያለኝን ግንኙነት በጥልቅ መመርመር የምፈልግበት ቦታ ላይ ነኝ። ለመረዳት እና ነጻነት ለመስጠት ይሞክራል ግን ትልቅ ፈተና ነው። ለእሱም ለኔም ፈታኝ ነው። በመሀላችን መስመር ማስመር ያለብን መስሎ ይሰማኛል። ‘አንድ ለአንድ የተወሰነ ትዳር አይደለም አንተም የራስህ ነገር አድርግ እኔም የራሴን መንገድ እከተላለሁ’ ብለን ብንወስን የሚቀል ይመስለኛል ግን እስካሁን የነበርበት ሁኔታ እንደዛ አይደለም።

እንደህይወት አጋር ካለን ግንኙነት ላይ ምንም ነገር ላለመውሰድ ያለውን ፍቃደኝነት እና ያለን ነገር ላይ ለመገንባት የሚያደርገውን ጥረት በጣም አከብራለሁ። ስለዚህ ግንኙነት በጣም የምወደው እና የማከብረው ነገር ይህ ነው።

ነገር ግን ተቃራኒ ጾታ ካለው ሰው ጋር በትዳር ውስጥ ሆኜ እንዴት የሁለትዮሽ ጾታ አፍቃሪነቴን ይበልጥ መረዳት እችላለሁ፣ አንድ ለአንድ ያልተወሰነ ትዳርን እንዴት ማስኬድ ይቻላል፣ ስርዓተ ጾታ እና የፆታ አገላለጾችን ደህንነት እንዲሰማው በሚያደርግ እና እኔን በማይገድበኝ መንገድ እንዴት መጠቀም አለብን የሚለው ፈታኝ ነው። በተለይም ስሜት ሲኖር ከባድ ነው፣ ስሜት ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ሊመጣ ይችላል። እንደዚህ አይነት ግንኙነት ውስጥ መሆን ሁላችንንም መመሪያ ወይም መጽሃፍ ኖሮን የምንወጣው ነገር አይደለም ግን የተለያዩ መፍትሄዎችን ለመፈለግ ቁርጠኛ ነኝ።

# የፍቅር አጋር የት ልናገኝ እንችላለን?
# የምንፈልገውስ ምን አይነት የፍቅር ግንኙነት ነው?

---

እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

---

**Abî Junior**
የ ሙሉ ሰዓት አፍቃሪ የሆነ ጊዜ ትኩረት እና እንክብካቤ የሚሰጠኝ እኔም የምሰጠው

Like Reply 22h

**NaNi FikR**
ታማኝ ኣፍቃሪ ግልፅ የስራ ሰው የፀዳ ፈታ ያለ...በዛ እንዴ😔

**በተስፋ ፍቅር ያሸንፋል**
በዚህ ህይወት ስንኖር በተቻለ አቅም ውስጣችን አሳምነን ነው አንዳንዴ ሰዎች ሳይቀበሉት ይሄን ህይወት ግን ግንኙነት ያደርጋሉ በዚህ መሃል ሁለቱም ተጎጂ ይሆናሉ ስለዚህ እንደኔ አስተሳሰብ በቅድሚያ ሁሉም የሚፈልገውን ከመማሰብ በፊት እራሱን መቀበል ውስጡን ማዳመጥ አለበት ባይ ነኝ ያኔ ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል እራስን ሳይቀበሉ ግን ሌላውን እቀበላለው ብሎ ግንኙነት መጀመር ከራስ አልፎ የሰውን ስሜትም ገደል መከተት ነው እና ልናስብበት ይገባል።

**በፍቅር ይሁን**
በየጊዜው የሚዳብር ነገር ሆኖ አጊኝቼዋለሁ።
ከዚህ ቀደም በነበሩኝ ጊዜያት እንደ ብዙ ሰው በማህበራዊ ሚዲያ ውሎ ጥያቄዎቾን ተቀብዬ ወይም ጥያቄዎቾን አቅርቤ ምቹ ሁኔታና መተማመን ላይ ያለሁ ሲመስለኝ እገናኛለሁ። (ይህ አሁንም እንደ ሁኔታው የቀጠለ ቢሆንም) አሁን ላይ እንደደረስኩበት ብስለት በተመሳሳይ የስሜት እና የመገናኘት ፍላጎት ካላቸው ጓደኞቼ ጋር አብረን ከመዝናናት ባለፈ አብሮ ቀናትን እስከመቆየት አድገናል። ነገር ግን በየ ካፌው በ ትራንስፖርት በምሽት ክለቦችና በስፖርት ቦታዎች መሻትና ፍላጎቶችን መግለፅ ቀላል ሆኗል። ይሔን ተከትሎ ስሜትን ደስታ መመገብ ላይ ጎበዝ ከሚባሉት መደብ ነኝ። በየትኛውም አጋጣሚ የማሳልፈውን የደስታ ግዜ ተራና አጭር እንዳይሆን ከእኔ የሚጠበቀውን ሁሉ አደርጋለሁ። በእኔ የተነሳ ተጓዳኜ ድብርት ውስጥ እንዳይወድቅም አስባለሁ��!

ለምን እንደዛ ዓይነት ሰዎች (ኢትዮጵያዊያን) ማግኘት እንዳልቻልኩ በእርግጠኝነት ምክንያቱን ባላውቅም ስገምት ግን ተስፋ ከመቁረጥና ሀገሪቷ ላይ በሕግም የተከለከለ ስለሆነና ሁሉም ነገር በድብቅ ስለሚሆን ምንም ባደርግ ብዙዎች ከአንዷ ጋር ስላለኝ ግንኙነት ስለማያውቁ ችግር የለውም ብለው ከማሰብ ይመስለኛል... "ሰው ምን ይለኛል" የሚል ጥያቄ ውስጣቸው አይፈጠርም ይሄ ደግሞ የሚሆነው ለራስ/ለሕሊና ካለመገዛት/ ክብር ከማጣት የተነሳ ነው።
የምፈልገው ከምንም በላይ ለራሷ ክብር ያላትና በራሷ የምትተማመን ብትሆን......👌

# የፍቅር አጋር የት ልናገኝ እንችላለን? የምንፈልገውስ ምን አይነት የፍቅር ግንኙነት ነው?

እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

Boney Ye Kele

በፍቅር ግንኙነት ውስጥ ወደ ህይወቴ ልጋብዘው የምችለው ሰው፦

፡፡ለህይወት ያለው አመለካከት ጤናማ እና ያልደበዘዘ በነገር ሁሉ አመስጋኝ እና ከራሱ ጋ የታረቀ የጋራ ደስታን ለመፍጠር የማይከብደው ፡፡
፡፡ ሃይማኖት፤ ባህል እና ቤተሰብ ከሚያመጣበት ግፊት እራሱን ሙሉ በሙሉ ነፃ ያወጣ እና ኩዊር በመሆኑ በአእምሮው እና በልቡ የማይወቀስ እና ከራሱ ጋር በዚህ ጉዳይ ፍፁም ሰላም የሆነ።
፡፡ ከኔ gender identity ጋር( i am non binary crossdresser) የፍቅር እና የወሲብ ተማርኮ ያለው እና የ ጀንደር ኢሹዎችን በአግባቡ የሚረዳ።
፡፡ ለኔ ባለው ስሜት እና ቦታ ፍፁም እርገጠኛ መሆን የሚችል ቸኩሎ የማያስቸኩል በጣም ደግሞ ዘግይቶ የፍቅርን እሳት የማያዳፍን።
፡፡ በዱልን በይቅርታ ለመሻር የማያመነታ እና ሰዎች ስለ ሰለሰው ከሚያወሩት ይልቅ ገለልተኛ ሆኖ በራሱ ሰውን የማወቅ እና የመረዳት ዝንባሌ ያለው።
፡፡ ፍፁም መድበስበስ በሌለው ሁኔታ ስለ እርሱ ማወቅ የፈለኩትን ነገር በግልፅነት የሚያሳውቀኝ። እርሱም ማወቅ የፈለገውን የሚጠይቅ።
፡፡ በህይወት ላይ በሚያጋጥሙት ፈተናዎች ውስጥ የኔ ከጎኑ መሆን ዋጋ እንዳለው የሚያምን።

Deve Love

በዋናነት፦መተማመንና መከባበር ወሳኝ ነው

Mes Robel

እስከአሁን ከሰማሁትና እኔም......
በዋናነት ከfb ጓደኝነት ይጀምርና
በውስጥ መስመር ማውራት
ይጀመራል "መተማመን" ደረጃ
ሲደረስ ስልክ መለዋወጥ ከዚያም
በአካል ተገናኝቶ......የሚሆን አይነት
ካልሆነና ካልቀጠለ መጀመሪያ
ከተዋወቅነው ዙሪያ ካሉ ሌሎች ጋር
የመተዋወቅ ዕድሉ ስለሚኖር ......😊
(እንዴት፤የት እና በምን መንገድ
ለሚለው በአጭሩ በFb፤Fbላይ እና
በሜሴንጀር 😀)

እኔ በበኩሌ እንዲኖረኝ ምፈልገዉ relationship...
- ዘላቂ የሆነ እንዲሆን እፈልጋለሁ
- በመነጋገር የምታምን እንዲሁም ፍፁም ፍቅር ያላት
- በሌሎች ተፅእና የማትወድቅ ( በቤተሰብ፣በጉደኛ ሌላም)
- ፍፁም እንዳልሆንን የምትረዳ እንዲሁም ባለን ነገር የምትረካ
- የውስጤን የምትረዳልኝ ጥሩ የህይወት አላማ ያላት
- ነገሮችን በብዙ አቅጣጫ የምትመለከት እና እና የቃላት ብቻ ሳይሆን የተግባር ሰው ብትሆን እና ፍፁም መተሳሰብ ያለበት በፍቅር የተሞላ ንፁህ የሆነ relationship እንዲኖረኝ ነው ።

በዚህ ሕይወት ውስጥ ያሉ ያወቅኳቸው በጣት የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ቢሆኑም እኔ እንደምፈልገው/እንደምመኘው/ ዓይነት relationship ውስጥ ያሉም የሚፈልጉምና ለሌሎች ምሳሌ የሚሆኑ ዓይነት ሰዎች አይደሉም ለማለት እደፍራለሁ።
ማንነታቸውን የተቀበሉና ለራሳቸው ክብር ያላቸው ሰዎችን እስካልተዋወኩኝ ድረስ ምንም አይነት ሪሌሽንሺፕ ከማንም ጋር አልፈልግም